# 'ተፈውሰሃል!' 'ተፈውሰሻል!' ሲባል ይጠየቃል።

ዘላለም መንግሥቱ

# ‘ተፈውሰሃል! ተፈውሰሻል!’ ሲባል ይጠየቃል። (ክፍል አንድ)

ፈውስ ርካሽ በሆነበት ዘመን፥ ፈውሰኞችም በበዙበት ዘመን፥ ‘ተፈውሰሃል!’ ‘ተፈውሰሻል!’ ሲባል ይጠየቃል።

ባለፈው ክፍል፥ ‘ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር!’ ሲሉ፥ ‘እውነት ብሎአል?’ ብሎ መጠየቅ ነውር አለመሆኑን አካፍያለሁ። ሰዎች አውቀው ወይም መስሎአቸው የልባቸውን፥ የስሜታቸውን በእግዚአብሔር ስም ሲናገሩ እግዚአብሔር የተናገረ መስሎአቸው ብዙዎች ይወናበዳሉ። ከሚወናበዱት ሰሚዎቻቸው የሚብሰው ደግሞ፥ እነሱም እግዚአብሔር የተናገራቸው መስሎአቸው ያንን ልምምድ እንደ ልማድ ወስደው ተወናብደው የሚያወናብዱት ናቸው። ይህ ከአዲሱ ጴንጤቆስጣዊነት ዋና ዋና ቀውሶች አንዱ ነው። ‘ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር!’ ሲሉ፥ እውነት ያንን ነገር የሠራዊቱ ጌታ እግዚአብሔር ብሏል? ወይስ ሰዎቹ ተናገሩት? ‘እውነት ብሎአል?’ ብሎ መጠየቅ ነውር እንዳልሆነ ነው ባለፈው ክፍል የተመለከትነው።

በዚህ ክፍል ደግሞ ሌላ እንካፈላለን። ያም የፈውስ ጉዳይ ነው። ፈውስን መጠየቅስ ነውር ነው ወይ? ‘ተፈውሰሃል!’ ሲባልም ቆም ብሎ ስለመጠየቅ ነው የማካፍለው፤ ይጠየቃል። ‘ተፈውሰሃል!’ ‘የሠራዊት ጌታ ፈውሶሻል!’ ሲሉ ‘እውነት፥ ፈውሷል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር?’ ብሎ መጠየቅ ድፍረት ሆኖ መቆጠር የለበትም። እውነት፥ የሠራዊቱ ጌታ እግዚአብሔር ፈውሷል? ወይስ የሰውየው ውሸትና የሰዎች ሞቅታ ነው ፈውሱን ያለ ያስመሰለው?

## የሞቅታ ፈውስ ምንጮች

የሞቅታ ፈውስ ያልኩት በማኅበራዊ ስነ ልቡና ሊቃውንት ዘንድ psycho-somatic healing የሚባለውን ነው። ይህንን psycho-somatic healingን ጨምሮ ሌሎችም ቃላት አሉ ማኅበራዊ ስነ ልቡናውያን የውሸት ፈውሶችን የሚገልጡባቸው ቃላት። ሦስቱን እንይ፤

1. ከላይ የጠቀስኩት Psycho-somatic healing አንዱ ነው፤ mind over bodyም ይባላል። አእምሮአችን የሌለ ፈውስን ለሥጋ ወይም ለአካል ሲነግርና ያንን ፈውስ ያለ ሲያስመስል ነው። አንዳንድ ሕመምተኞች ‘ፈዋሽ’ ያሉት ሰው ቃል ሲናገር ወይም በእነርሱ አባባል፥ ሲያውጅ አእምሮአቸውን ያሳምናሉ፤ ቃል ሥጋ እንዲለብስ ወይም በሥጋ እንዲከሰት (manifest እንዲያደርግ) ይጠብቃሉ። አእምሮአቸው በተራው በሰውነታቸው ስሜትን ይፈጥራል። ለቅጽበት (ቅጽበት ይሰመርበት) የተፈወሱ ይመስላቸዋል። መስሎአቸው ሊመሰክሩ ሁላ ይችላሉ። መድኃኒታቸውንም ሊጥሉ ይችላሉ። ግን ከሕመማቸው ጋር ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ከዚህ በፊት ሲውዶሳየሲስ ወይም የውሸት እርግዝና ስለሚባል አባዜ ከአንዲት በዚህ ነገር ውስጥ ካለፈች እኅት ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌ ነበር። ያ እና ይህ Psycho-somatic healing ወይም የሞቅታ ፈውስ ተቀራራቢ ልምምዶች ናቸው።

2. ሁለተኛው፥ Peer pressure ወይም group dynamics የሚባለው ነው። ይህ ብዙ ጊዜ በብዙዎች ግፊት ወይም ገፋፊነት የሚፈጠር ጊዜያዊ ወኔ፥ ወይም በዙሪያ እየሆነ ካለው ነገር ጋር የመመሳሰልና የመንጎድ ልምምድ ነው። ብዙዎች ተፈወስኩ ብለው ሲጮሁ አብሮ መጮህ፥ ሲገነደሱ አብሮ መገንደስ፥ የሚሉትን ማለት፥ በራስ ጭንቅላት ሳይሆን በሰባኪው ጭንቅላት ወይም ሰባኪው በሚያሳስበውና በሚያነሣሳው የጉባኤ ጭንቅላት በጋራ ማሰብ ነው። የጎራ ወይም የመንጋ አስተሳሰብ ማለት ነው። ለመመሳሰል ተብሎ የሚገቡበት ማጥ ነው። ሌሎችን ለማስደሰት ብሎ ሳይፈወሱም ተፈወስኩ የማለት ውሸትና ቅዠት ነው።

3. Suggestibility ወይም hyper-suggestibility ደግሞ አንድ ነገርን መናፈቅና ይሆናል ብሎ በእርግጠኛነት ከመጠባበቅ የተነሣ የሚጠበቀው ነገር የሆነ የመምሰሉ ልምምድ ነው። ከpsycho-somatic healing ጋር ይቀራረባል፤ ግን ይህ ከፈውስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች (ለምሳሌ በልሳን ከመናገር) ጋር ይቆራኛል። አንድ ሕመምተኛ ፈውስ አለ ወደ ሚባልበት ጉባኤ ሲሄድ ፈውስን ጠብቆ ነው። ተፈወስን የሚሉ ሰዎች ሲመሰክሩ ተደጋግሞ የተሰሙ ነገሮችንና ምልክቶችን ይህም ሰው በአካሉ ወይም በስሜቱ እንዲሰማው መጠበቅ ይጀምራል። የሆነ ነፋሻ ሽውታ፥ ኮሽታ፥ ንዝረት፥

ሙቀት፥ ቅዝቃዜ፥ ምንም ነገር ይጠብቃል። በጥፍሩ ቆሞ ነው የሚጠብቀው። ይህ ከልክ ያለፈ መጠበቅ ነው hyper-suggestibility የሚባለው። ያንን ኮሽታ፥ ንዝረት፥ ሙቀት፥ ወዘተ፥ በጥቂቱ የሚመስል ነገር ከተሰማው 'ፈውስ' ነው ብሎ፥ በስሜት ሰክሮ መጮህ ነው። ከልክ ካለፈ መመኘትና መጠበቅ የተነሣ ያ ነገር በውስጣችን እስኪሰማንና እስኪታየን እንደርሳለን። በገሃዱ ዓለም ግን የለም። የምንጠብቀውን የምንጓጓውን ነገር ምናባችን የሚያስበውን ነገር እስከንሰማው እንደርሳለን።

## ፈውሰኞች

ፈውስ መኖሩን አምናለሁ። እግዚአብሔር ጸሎትን የሚሰማና የሚመልስ አምላክ ነው። ፈውስ ቅጽበታዊም በሂደትም የሚሆን ነገር ነው። ፈውስ መብት ወይም ሥልጣን አለመሆኑንም አውቃለሁ። ፈውስ መብትና ሥልጣን ነው የሚለው ትምህርት ከቃለ እምነት የስሕተት ትምህርት ጋር የተያያዘ የአዲሱ አስተሳሰብ (New Thought) ትምህርት ነው። የብልጽግና ወንጌል፥ የጤንነት ወንጌል፥ ወዘተ፥ የሚባሉ ብልጽግናም፥ ጤንነትም፥ ወንጌልም ያልሆኑ በሽተኛ ትምህርቶች ናቸው ይህንን የሌለና ኖሮም የማያውቅ መብት የሚያስጨብጡን። ጤንነትና ብልጽግና ልክ እንደ ደህንነት ስንድን የምንቀዳጀው መብት አይደለም። ቢሆንማ ኖሮ፥ ማንም ክርስቲያን ጌታን ጌታው አድርጎ ሊከተለው ሲጀምር መታመም የለበትም። የሕመም መኖር ቀርቶ መታሰቢያውም መኖር አልነበረበትም። ልክ እንደ መዳናችን ሁሉ ፈውሳችንም ስንድን የምንቀበለው ስጦታ መሆን ነበረበት። በዳነ ሰው አካባቢ ምንም የሕመም ጉዳይ መነሣት አልነበረበትም። በእውነቱ፥ ፈውስም መነሣት የለበትም፤ የፈውስ ኮንፈረንስም መኖር የለበትም። ቀድሞውኑ የማንታመም ከሆንን፥ አንፈወስማ! የማንታመም ነንና ፈውስ ምን ያደርግልናል? ግን አይደለም። በውሸት ፈውስ አካላቸው የተጎዳና ልባቸው የተሰበረ፥ መንፈሳዊ ሕይወታቸውም የተበላሸ ብዙ ናቸው። ስለዚህ፥ 'ፈውስ!' ሲባል ቆም ብለን መጠየቅ አለብን።

ፈውስን በተመለከተ፥ የአንዳንድ 'ትልልቅ' ሰዎች አገልግሎቶች በትልልቅ 'ተአምራት' የታጀቡ ናቸው ብለን እንድናስብ ተደርገናል፤ ወይም ተሠርቶብናል። 'በተአምራት!' ማስታወቂያዎቻቸው አሁን አሁን ጋብ እያሉና እየሰከኑ መጡ እንጂ፥ 'የድንቅና የተአምራት ፕሮግራም! ዕውሮች ይበራሉ! ደንቆሮዎች ይሰማሉ! ዲዳዎች ይዘምራሉ! አንካሶች ይዘላሉ! ሙታን ይነሣሉ!' ወዘተ፥ እያሉ በድፍረት ጽፈው ይለጥፋሉ። አንካሶች ወይም ዕውሮች ሲመጡ ግን ዞር ብለው አያዩአቸውም። እየቆየ እየቆየ ሰከን እያሉ መጡና ወደ ውስጥ ደዌ እስፔሻሊስትነት ተቀየሩ። ዕውሮች ይበራሉ፥ አንካሶች

ይዘልላሉ ማለት ቀረና፥ የደዌ ዓይነት መጥራት ተጀመረ፤ የማይጠሩት የኩላሊት ጠጠር፥ የሳንባ፥ የልብ፥ የግራ ጎን ሕመም የለም። አንዴ አገለግል በነበርኩባት ቤተ ክርስቲያን፥ ሁሌ፥ ‘ግራ ጎንህን የሚያምህ’ የሚል ወንድም ነበረ። ሁሌ ያንን ከማለቱ የተነሣ፥ ‘ግራ ጎን’ እየተባለም ይጠራ ነበር።

እነዚህን ፈውሰኞች፥ ‘የተፈወሱትን አሳዩን፥ አቅርቡልን’ ሲባሉ፥ እነሱም ምልክቶቻቸውም የሉም። ለምን? ‘ለምን?’ ብሎ ማን ይጠይቃቸዋል? በተለይ የ30 እና 40 ዓመት አገልግሎት ብለው ካከበሩ በኋላ ምን ተብሎ ይጠየቃል? ነውር አይደል እንዴ? 40 ዓመት ማክበር ለምን ልዩ እንደ ሆነ አላውቅም። ለምን ሽልማት መቀበል እንዳስፈለገም አላውቅም። ሙሴ፥ ወይም ጳውሎስ 40 ዓመት ካገለገሉ በኋላ ድግስ ተደግሶ ሜዳልያ ቢቀርብላቸው ምን ያደርጉ እንደነበር በምናቤ ማሰብ እችላለሁ። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ጥያቄ ሲጠየቁ ለምን ይከፋቸዋል? መጥጠየቅንስ ለምን አጥብቀው ይጠላሉ? የሚብሰው ደግሞ፥ እነሱ ሲጠየቁ፥ ‘ለምን ተጠየቁ?!’ ብለው ቁጭ ብድግ የሚሉ ቲፎዞዎቻቸው ናቸው።

ከዚህ በፊት፥ ‘ቤኒ ሂን እና ‘ፈውሶቹ’’ በተሰኘች አጭር ጽሑፌ ላይ አንድ ጉዳይ አካፍዬ ነበር። ሃንክ ሃነግራፍ የተባለ የምካቴ ክርስትና አገልጋይ ቤኒ ሂን የተባለ ፈውሰኛን፥ ‘እውነተኛ ድውያን የነበሩና እውነተኛ ፈውስ በአንተ የፈውስ ስጦታ በኩል የተቀበሉ 3 ብቻ ሰዎች አመልክተኝ።’ ብሎ ጠይቆት እንደ ነበር። ቤኒ ሦስት ሰዎችን ሰጠው፤ የሰጠው ሦስት ሰዎች ፈውሶች የውሸት መሆናቸውን ማረጋገጡን ሃንክ እንደተናገረ ያካፈልኩበት ነበር ያ ጽሑፍ። አንዱ ፈውስ ሕመሙም ፈውሱም የሌለ፥ ሌሎቹ ሕመሞቹ ያሉ ፈውሶቹ ግን የሌሉ ነበሩ።

## የኤድስ ፈውሶችና ፈውሰኞች

ልክ ሃንክ እንደጠየቀው፥ እኔም ጠይቄ አውቃለሁ። እኔ የጠየቅኋቸው ስለ ጠቅላላ የውስጥ ደዌ ፈውስ ሳይሆን በተለይ ስለ ኤድስ ፈውስ የተናገሩ የአገራችን ፈውሰኞችን ነው። ስለ ኤድስ ፈውሳቸው ማረጋገጫ ነው የጠየቅኋቸው። ሌሎቹን ስለ ሌሎች ነገሮች ጠይቄ አውቃለሁ፤ እነዚህን አራቱን ግን ስለ ኤድስ ፈውሳቸው ብቻ ነው የጠየቅሁት። ኤድስን የመረጥኩት በምክንያት ነው። ኤድስ እንደምናውቀው በሽታ አይደለም። ኤድስ በመድኃኒት ወይም በቀዶ ጥገና የሚጠፋ ወይም ሰለባዎቹ ቆይተው ቀስ በቀስ እየተሻላቸው፥ የሚያገግሙትና የሚድኑት ሕመም አይደለም። ኤድስ ሕመም ሳይሆን መቅሰፍት ነው ማለት ይቻላል።

አንድ ሰው ከኤድስ ዳነ ከተባለ ከማይድኑት መቅሰፍት መዳን ስለሆነ ፈውሱ ትልቅ ፈውስ ነው። ለዚህ ነው ኤድስን የመረጥኩትና እነዚህን አራት ሰዎች የጠየቅኋቸው። በጠየቅኩበት ዘመን ቅደም ተከተል፥ *መጋቢ ሞገስ መንግሥቱ፥ መጋቢ ዶ/ር ዳን ስለሺ፥ መጋቢ ሰይፉ ከበደ፥ እና መጋቢ ደሳለኝ ኢተፋ* ናቸው። እኔ ሐሰተኛ ነቢያትን እና ሐሰተኛ ሐዋርያትን ስጠቅስ፥ ወይም ማናቸውንም የስሕተት ትምህርቶችንና ልምምዶችን ስገልጥ አሳቾቹን በስም እናገራለሁ። ከስሕተት ልምምዶች መካከል አንዱ የውሸት ፈውስ ነው። ስሞችን በየጊዜው መጥቀሴ ብዙ ሰዎችን የሚያስቆጣ ነገር ሆኖ ተገኝቶአል። የሚገርመውና እንዲያውም የሚያሳዝነው ነገር፥ ያልተፈወሱት ሰዎች ሳይፈወሱ፥ 'ተፈውሳችኋል!' መባላቸው ያላስቆጣቸው ሰዎች፥ የውሸት ፈውሱን ያከናወኑትን ሰዎች መጥቀሴ ማስቆጣቱ ነው። ከላይ ቲፎዞዎች እንዳልኳቸው ሰዎች ማለት ነው። ማስቆጣት የነበረበት እኮ የውሸቱ ፈውስ መሆን ነበረበት። በተገላቢጦሽ፥ 'አንተ ማን ሆነህ ነው እገሌን የምትናገር?' የተባልኩባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው።

*መጋቢ ሞገስ መንግሥቱ፥* ሞገስ በቅርብ የማውቀው ሰው ነው። እኔ በመጀመሪያ የክርስትና እምነቴ ወራት ባደግሁባት በኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት ያገለግል በነበረ ጊዜ ነው ይህ የሆነው። ሞገስ፥ 'ተፈወሰ' ያለውን ሰው፥ *መጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስሕተቶች* በተሰኘው መጽሐፌ፥ አስተውሎት በተሰኘው ምዕራፍ፥ የኤድስ 'ፈውስ' በሚል ንዑስ ርእስ የተጻፈው ታሪክ የተጻፈበት የውሸት ፈውስ ታሪክ ነው። እዚያ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኩን በስፋት ጽፌዋለሁ። 'ፈውሱ' የሆነው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1989 ዓመተ ምሕረት በታኅሣስ ወር ነው። ይህንን፥ 'ተፈወሰ' የተባለ ሰው ቃለ ምልልስ ሁሉ አድርገንለት፥ በቀጣይ በሁለተኛው የቃለ ምልልስ ቀጠሮ ማስረጃዎቹን ይዞ እንዲመጣ ተቀጣጥረን የውኃ ሽታ ሆኖ ጠፋ። ማስረጃዎቹ ያልናቸው ከኤድስ ስለመፈወሱ የሐኪም ማረጋገጫ ጭምር ነው። ኋላ ስንሰማ፥ 'ተፈውስኩ' እያለ ድራማ መሥራቱ የተለመደ ማታለያውና ገንዘብ ማግኛው መሆኑን ነበር የተረዳነው። ይህ ፈውሱ እውነት ባይሆንም ተፈወስኩ ካለው ሰው ጋር በቅርብ የተገናኘንበት አጋጣሚ ነበረ። ታሪኩን ባልኩት መጽሐፍ ተመልከቱት።

*መጋቢ ዶ/ር ዳን ስለሺ* በፈረንጆች አቆጣጠር በ2003 በካናዳ በቫንኩቨር ከተማ በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ሲሰብክ የሰማሁትና፥ 'ከኤድስ ተፈወሰ' ስላለው ሰው፥ 'ተፈወሰ' የተባለው ሰው የነበረባትን በሌላ የካናዳ ከተማ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ጠይቄ ነበር። መጋቢው ፈውሱን አረጋግጦ እንደነበር ስጠይቀው አላረጋገጠም፤ ግን እርሱ ራሱም ፈውሱን አምኖ ተቀብሎአል። እንዴት እንዳልጠረጠረ ወይም እንዴት እንዳመነ ስጠይቀው፥ በሽተኛውን በግል ካጫወተው በመነሣትና ሲመረመር የኤች አይ ቪ ካውንቱ ወይም በደም ሴሎች ውስጥ

የሚቆጠረው የቫይረስ መጠን እንደቀነሰ በመናገሩ ነው። ይህ ‘ካውንት’ የሚባለው ነገር ደም ወስደው ሲመረምሩ በደም ውስጥ ያለው የቫይረሶቹ ቁጥር ወይም መጠን ሲጨምርና ሲቀንስ የሚሆነው ነገር ነው። ይህ ቁጥር እንደ ሰዎቹ የሰውነት አቋምና ጤንነት አንዳንዴ ይጨምራል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይቀንሳል እንጂ አይጠፋም። መጋቢውን ለምን አስመርምሮ ማረጋገጡን እንዳላሰበበት ስጠይቀው፥ የአገራችንን ባህል ጉዳይ አውስቶ፥ የሰዎቹን ስሜት የሚጎዳ መሆኑን እና ነገሩን ወደ መንፈሳዊነት በማስጠጋት ደግሞ፥ ይህንን መጠየቅ፥ ሰውየው አምኖ የተቀበለውን እምነቱን መፈታተንና ፈውሱን ማበላሸት መሆኑን ነበር የነገረኝ። የቫይረስ መጠንና ቁጥር መቀነስ እንጂ እዚህ የተረጋገጠ ፈውስ የለም።

**መጋቢ ሰይፉ ከበደ** ተአምራት እና የፈውስ ኪዳን በተባሉ መጽሐፎች ውስጥ መጋቢው ካያቸው ተአምራት ዝርዝር ውስጥ የኤድስ መመታት ወይም ሰዎች ከኤድስ መፈወሳቸውም ይገኝበታል። የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ባልጠራጠርም የሰማኋቸውና የገጠሙኝ የኤድስ ፈውሶች ሁሉ ውሸት ሆነው ስላገኘሁ ተጨባጭ መልስ ለማግኘትና የተፈወሱት ሰዎች ፈውስ እውነት ከሆነና ተፈዋሾቹ ፈቃደኛ ከሆኑ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከኤድስ የተፈወሱ አንድ ሁለት ሰዎችን ስምና አድራሻ እንዲሰጠኝ ደራሲውን መጋቢ ጠይቄ ነበር። ያኔም እስከ ዛሬም ድረስ መልስ አላገኘሁም።

**መጋቢ ደሳለኝ አላቤ** በ2012 በሌችብሪጅ ካናዳ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሲሰብክ፥ ከዚያ ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ በነበረው አገልግሎቱ ሦስት ሰዎች ከኤድስ መፈወሳቸውን ተናገረ። በዚያ ጉባኤ ቆይቼ ልጠይቀው ስላልቻልኩና መሽቶ ወደ ከተማችን ስለተመለስን፥ እርሱም ከካናዳ ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ በደብዳቤ የሰዎቹን ስምና አድራሻ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት። ‘ተፈወሱ’ የተባሉት ሰዎች ደግሞ እኔ ተወልጄ ካደግሁበት ከተማ ብዙም ስለማይርቅ፥ እኔም ባልችል በሰዎች እንዲረጋገጥ ማድረግ እችላለሁና የተፈዋሾችን ስም እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት። ከእርሱም የሰዎቹን ስምና አድራሻ ብቻ ሳይሆን፥ ለጻፍኩለት ደብዳቤዬ መልስም አላገኘሁም።

## ይጠየቃል

እነዚህ ለፈውሰኞቹ ያቀረብሁት ጥቂት ጥያቄዎቼ ሲሆኑ ሁሉም በኤድስ ብቻ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ፈውስን መጠርጠር እውነተኛ ፈውስ የለም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ይፈውሳል። ፈውሱ ደግሞ ድብቅ አይደለም። ይህ ሆኖ ሳለ፥ ‘እስኪ ማስረጃ?’ ሲባል፥ ለምንድር ነው እንደ ነውር የሚታየው? ለምንድር ነው መጠየቅና መጥጠየቅ የሚያስፈራው? በውሸት ፈውስ እኮ ሰዎችን እንጂ እግዚአብሔርን ፈዋሽ

ማስመሰል አንችልም! ፈውስ ድብቅ ነገር አይደለም። ለተፈዋሹም፥ ለሌሎችም ስውር አይደለም።

ፈውስ ብቻ ሳይሆን፥ ተአምርም እንዲሁ ድብቅ አይደለም። ያልረዘመ አንድ እግር በመጀመሪያ 'ማስረዘም' እና ያንን የረዘመውን እንዲያህል ደግሞ ሌላኛውንም 'ማስረዘም' ምን የሚሉት ማጃጃል ነው? ፊልጶስ ሲራንሶ፥ ኢዩ ጩፋ፥ እና ሀብታሙ ጳውሎስ የተባሉ ሐሰተኛ ነቢያት ይህን ለማድረግ ሞክረዋል። ማንን ለማታለል እንደሞከሩ ቢጠየቁ መልስ ይኖራቸው ይሆን? የላቸውም። በውሸት ግን ቁመት ያስረዘሙ መስለዋል። ይህ እኮ መጃጃልና ማጃጃል ሳይሆን ውሸት ነው፤ ቅጥፈት ነው። ውሸት ደግሞ ኃጢአት ነው። የሰዎች ቁመት ሲረዝም፥ የረዘሙትን ሰዎች ቁመታቸው ስንት ኢንች ወይም ስንት ጫማ እንደረዘመ መጠየቅ ለምን ነውር ሆኖ ታየ? ቁመታቸው ሲረዝም ልብሳቸውስ እንዴት አላጠረም ብሎ መጠየቅ ለምን ከበደ? አንድ እግራቸው ከረዘመ በኋላ በአንድ ረጅምና በአንድ አጭር እግር ተመላልሰው እንዲያሳዩ መጠየቅ ለምን የማይታሰብ ሆነ? ይጠየቃል እኮ!

ሐሰተኛ ነቢይ ኢዩ ጩፋ በመድረክ ላይ ያቆማትን አንዲት ሴት መጀመሪያ ዓይኗን አሳውሮ ቀጥሎ እንድታይ 'ያበራው' እኮ ድራማ ነው! የምታይ ጤነኛ ሴትን ሲጀመር ለምን 'አሳወረ?' ለነገሩ የታወረች መሰለች እንጂ አልታወረችም፤ ይህ አጭበርባሪ ይህን ያደረገው ተአምር ሠሪ ለመምሰል ነው። እነዚህን መጠየቅ ለምን ነውር ሆነ? 'እውነት ሆነ?' ተብሎ ይጠየቃል እኮ! የነማን እግር በእውነት ረዘመ? እውነት መርዘም ነበረበት? እነማን ከኤድስ ተፈወሱ? እነማን ከሞት ተነሡ? የነማን ጣት ቷ! ቷ! ቷ! ብሎ በቀለ? ብሎ መጠየቅ ለምን ያስፈራል? ልጅ ትወልዳላችሁ ተብለው ለምን አልወለዱም? ብሎ መጠየቅ ለምን ተነወረ? እግዚአብሔር ፈዋሽ እና ተአምር አድራጊ አምላክ መሆኑን ሳንረሳ፥ ሰውን መጠርጠር እኮ እግዚአብሔርን መካድ አይደለም! የአንዳንዶቹ አገልጋዮቻችን 'ግዙፍነት' የሚያንገዳግደን ስለሆነ፥ የሚወድቁብን ስለሚመስለን የሚሉትን ምንም ሳንጠይቅ እንቀበላለን። እነሱን አለመቀበል ጌታን አለመቀበል፥ እነሱን መካድን እግዚአብሔርን መካድ ያስመስሉብኛል፤ ለምን? ልዕለ ሰብ መስሎ ለመታየት!

ፈውስ እኮ በሰውነታችን የምናውቀው ነገር ነው። ጌታን ዳስሳ ስለተፈወሰችው ሴት ማርቆስ ሲጽፍ፥ *ወዲያውም የደምዋ ምንጭ ደረቀ ከሥቃይዋም እንደዳነች በሰውነትዋ አወቀች።* (ማር. 5፥29) ነው ያለው። በሰውነትዋ አወቀች። ይህኛው ለሌሎች ላይታይ ይችላል፤ ራስዋ አወቀች። ዕውር ካየ እኮ እያየ ነውና አይጠየቅም፤ አይጠረጠርም። እራሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ያውቁታል። ያለ መሪ እያየ እየሄደ ነዋ! በርጤሜዎስን፥ 'እውነት ታያለህ? እውነት እየታየህ ነው የምትራመደው?' ማን ይላል?

ሸባ አልጋውን ተሸክሞ ሲሄድ ማን ይጠይቃል? ማን ይጠረጥራል? እንደ ልውስ የተከመረ ሰውነት እኮ ቆሞ እየተራመደ ነው! እነዚህ አይጠየቁም።

የሚያስጠይቀው ውሸታሙ ነገር ደግሞ ቢጠየቅስ? ምን ችግር አለው? ለምን ነውር መሰለ? ለምን ነውር ሆነ? የሌለ ፈውስ ሲነገር፥ ያልኖረ ፈውስ ሲታወጅ፥ ተፈውሳችኋል ሲባል፥ ተፈውሰሃል፥ ተፈውሰሻል ሲባል ይጠየቃል። ይጠየቃል።

# 'ተፈውሰሃል! ተፈውሰሻል!' ሲባል ይጠየቃል። (ክፍል ሁለት)

በክፍል አንድ ስለ ፈውስ ጥያቄ የሌለ፥ ያልኖረ ፈውስን ፈውስ ስለሚያስመስሉ ሦስት ነገሮች ተናግሬ፥ አራት የውሸት የኤድስ ፈውሶችንና ፈውሰኞችንም ጠቅሼ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ መጀመሪያ የጻፍኩት ከ30 ያህል ዓመታት በፊት፥ መንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች በተሰኘው መጽሐፌ ውስጥ፥ 'የፈውስ ቀውስ' በሚል ንዑስ ርእስ ስር ነው። ከዚያ ወዲህ በመጣጥፎችና በቪድዮዎችም በተደጋጋሚ አንሥቼዋለሁ። አሁንም እየተናገርኩበት፥ እየጻፍኩበት እገኛለሁ። ለምን? ችግሩ እስካለ ድረስ፥ ቀውሱ እስካለ ድረስ አንዳንድ ጉዳዮች ሳያሠልሱ ይነገራሉ። የውሸት ፈውስ ከእነዚህ ቀውሶች መካከል አንዱ ነው። የውሸት ፈውስ ቅዱሳንን አብዝቶ የጎዳ፥ በፈውስ ፈንታ ራሱ በሽታ የሆነ ጴንጤቆስጣዊ ልምምድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፈወሱ ሰዎች ፈውሳቸው የውሸት ፈውስ አልነበረም። 'ነው? ወይስ አይደለም?' ተብሎ የሚያጠራጥር እንኳ አልነበረም። 'ተፈውሰዋል' ተብሎ ገሚሱ ተፈውሰው ገሚሱ ያልተፈወሱም አልነበሩም።

ተአምር ሲሆንም፥ (ፈውስ ያልሆነ ተአምር) ሙሉና እውነተኛ ተአምር እንጂ ጎዶሎ ወይም ምትሐት አልነበረም። ጌታ በአካላት ላይ የሠራቸው ሁለት ዓይነት ነገሮች ፈውስ እና ተአምራት ናቸው። ፈውስና ተአምር አይምታቱብን፤ የታመመ ሲድን፥ ድውይ ሲፈወስ፥ የተበላሸ አካል ሲሰምር፥ ጤና ሲሆን ፈውስ ነው። የሌለ አካል ሲፈጠር ደግሞ ተአምር ነው፤ ዓይን ሲበራ ፈውስ ሳይሆን ተአምር ነው። የታመመ ዓይን ሳይሆን የሌለ ነው የተፈጠረው። ጉንድሽ ሰው እጅ ወይም እግር ሲኖረው ተአምር ነው። የታመመ እጅና እግር አይደለም የዳነው፤ የሌለው ነው የተፈጠረው። ሰው ከሙታን ሲነሣ ተአምር ነው፤ በጌታ እጅ ሦስት ሰዎች ከሞት ተነሥተዋል፤ በጳውሎስም በጴጥሮስም እጅ ሌሎች ሁለት የሞቱ ሰዎች ተነሥተዋል። ይህ ተአምር ነው። ፈውስና ተአምር የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

## 'ስላላመኑ ነው!' የሚሏት ዘፈንስ?

ተአምራት፥ ከተአምራት ጋር ፈውስም ተጨምሮ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ተአምራትና ፈውሶች የተከማቹባቸው ሦስት ልዩ ዘመናት አሉ፤ ኋላ አነሣዋለሁ። እዚህ ግን ስለ ፈውስ እና ውሸታም ፈውስ ልቀጥል። ዛሬ ለምን ጥያቄ በጥያቄ ሆንን? ለምን የውሸት ፈውስ በውሸት ፈውስ ሆንን? ለምን፥ 'ስላላመኑ ነው ያልተፈወሱት' በዛ? ይህቺ፥ 'ስላላመኑ ነው ያልተፈወሱት' የሚሏት ነገር ሲያፍሩ መሸሻ ሲያጡ የሚመዝዟት ካርታ ናት። አሳዛኙ ነገር ግን፥ ታማሚዎቹ አለመፈወሳቸው ሳያንሳቸው እምነት ያጡ የመሆናቸው ጉዳተኞችና ሰለባዎችም ሲሆኑ ነው። ውሸታሞቹ ፈውሰኞች ሕዝቡን፥ ይህን ያልተማረና ለመማር የማይፈቅድ ሕዝብ እየደለሉ፥ እየሸወዱ ያልፉታል።

ጌታ በሰዎች አለማመን ምክንያት ተአምር አለማድረጉንም ይጠቅሳሉ፤ *በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።* የሚለውን የማቴ. 13፥58ን ጥቅስ ይጠቅሳሉ። ስለዚያ ጥቅስ አራት ነገሮችን እንይ፤

1ኛ፥ የእርሱ ተአምር ማድረግ ሥልጣን በሰዎች ፈጽሞ የሚደገፍ አይደለም፤ በሰዎች ማመንና አለማመን የሚደገፍ፥ የሚወሰን፥ የሚገደብ አይደለም። ከሆነ አምላክ አይደለም፤ አምላክ በምንም አይወሰንም፤ አይደገፍም።

2ኛ፥ ተአምር ካደረገም ለራሱ ክብር ነውና ማድረግ እንዳለበትና እንደሌለበት ሌላ ማንም አይወስንም፤ አይቀምርም። በራሱ ፈቃድ ነው የሚያደርገው።

3ኛ፥ *በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።* ነው የተባለውና ባለማመናቸው ምክንያት ምንም አላደረገም ሳይሆን ጥቂት አድርጎአል። ብዙ ነው ያላደረገው። ስለዚህ፥ ባያምኑም እንኳ ተአምሩ ተደርጓል ማለት ነው። 'ስላላመኑ ነው ያላደረገው' ብሎ መሸወድ አይቻልም። ባያምኑም እንኳ አድርጓል።

4ኛ፥ ያ ጥቅስ የተጻፈበት ቦታ እኮ እርሱን እንደ ተራ ሰው ብቻ የተመለከቱት ያደገባት የናዝሬት ሰዎች ከተማ ወይም ቦታ ነው፤ ሰዎቹም ያደገባት የናዝሬት ሰዎች ናቸው። እርሱን ጭራሽ አልተቀበሉትም፤ እንደ ነቢይ እንኳን አልተቀበሉትም። በእርሱ ስላላመኑና እርሱን ስላላመኑት፥ ስላልተቀበሉት ነው ብዙ ተአምር ያላደረገው። አንዳንድ ሰዎች ከእርሱ ይልቅ ምልክቱን ይፈልጋሉ። ከተአምር አድራጊው ይልቅ ተአምሩን ይሻሉ፤ ልክ ዛሬም ከገበታው ጌታ ይልቅ የጌታውን ገበታ እንደሚፈልጉት።

ጉዳያቸው ከገበታው አድራጊ ጋር ከሆነ ገበታው ቢኖርም ባይኖርም ጉዳያቸው አይደለም። ከተአምሩና ፈውሱ ጋር ብቻ ከሆነ ግን የነገሩ መኖር እንጂ የእርሱ መገኘት አይደለም። እንጀራ ሲበሉ፥ ‘እናንግሠው!’ ይሉና፥ ‘ሥጋዬን ያልበላ’ ሲል፥ ‘አስጨናቂ’ ብለው ስም ያወጡልሃል። እነዚህ ተአምር ቢደረግ በተአምሩ የሚደሰቱ ሆነው ከአድራጊው ጋር ግንኙነት አይፈልጉም። የናዝሬት ሰዎች እንደዚያ ነበሩ።

እዚህ፥ ‘ያልተፈወሱት ስላላመኑ ነው’ የሚሏቸው ሰዎች እኮ ክርስቲያኖች ናቸው፤ ያመኑ፥ በጌታ የሚያምኑ ሰዎች ናቸው። የማያምኑ ሰዎች ቢሆኑ የማያምኑ ሰዎች ናቸው ሊሉ ምናልባት ይችሉ ይሆናል። ያንን ሲሉም ከጌታ ጋር ራሳቸውን እያስተያዩ መሆናቸው መሰመር አለበት። አድራጊዎቹ ያንን እየሆኑ ናቸዋ! አንድ ፈውሰኛ፥ ‘ስላላመነ ነው ያልተፈወሰው’ ቢል፥ በማን ስላላመነ? በጌታ ወይስ በፈውሰኛው? እንዴት ነው ያ ሰው፥ በጌታ አላመነም የሚባለው?

ካልተፈወሰው ሰውዬ ቀጥሎ ያልፈወሰውን ሰውዬ ብንጠይቅስ? ይህ ስላላመነ ነው ያልተፈወሰው፤ እሺ፤ ሌላስ አምኖ የተፈወሰ አለ? ከኖረስ ሊያሳየን ይችላል አምኖ የተፈወሰ ሰው? ከሆነ ምኑ ነው የፈወሰው? እምነቱ ነው? ወይስ ፈውሰኛው? እምነቱ ከሆነ ፈውሰኛው ምን ሊሠራ እዚያ ተገኘ? ይህንን ጥያቄ ይቀበለዋል? የሚታመነው ነገር እርሱ ነው? የእርሱ ቃል ነው? የጌታ ቃል ነው? ወይስ ጌታ ነው? የእርሱ ሚና ከቶ ምንድር ነው? አያችሁ የሚጫወቱባት የቃል እምነት የምትባለው ኑፋቄ ጨዋታዋ ይህች ናት። ፈውሰኛው ሰዎቹ የተፈወሱ ከሆኑ ወይም ከመሰሉ፥ ዝናውን፥ ስሙን፥ ክብሩን፥ ክሬዲቱን ለመውሰድ ይጋጋጣል። ካልሆኑ ደግሞ ተጠያቂ አይሆንም፤ ተጠያቂዎቹ እነርሱ ያልተፈወሱት ሰዎች ናቸው። አለመፈወስ ሳያንሳቸው፥ እምነተ ቢስ ተደርገው አስይዘው ተበልተው ይመለሳሉ። ነገሩ ቁማር ነዋ! ባለማመናቸው ብዙ ተአምራት ያልተደረገባቸው ከተማዎች መኖራቸውን እንጂ ባለማመናቸው ምክንያት ሳይፈወሱ የቀሩ ሰዎች እንዳልነበሩ መቀበል አይፈልጉም።

ከተፈወሱ ወይም ተአምር ከተፈጸመላቸው ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ጨርሶ በጌታ የማያምኑ ሰዎች እንኳን ነበሩ እኮ! ዮሐ. 9 ይመስክር። ይህ በዮሐ. 9 የምናገኘው ሰው ከቶም አማኝ አልነበረም፤ እንዲያውም ሰውየው ፈውስም፥ ተአምርም አልጠበቀም፤ አልለመነም፤ እንደ በርጤሜዎስ፥ ‘የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ!’ እያለ አልተጣራም። ኋላ ነው የሆነለት ነገር ተሰምቶ፥ ወደ ፈሪሳውያን ተወስዶ፥ ተጠይቆ፥ ተመርምሮ፥ ወላጆቹ ተመርምረው ወደ ውጪ ሲያወጡት፥ (ምናልባት ከመቅደስ ወይም ከምኵራብ) ዮሐ. 9፥35-36፥ *ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ ሲያገኘውም፡- አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው። እርሱም መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ።* አያውቀውም የፈወሰውን፤ ሲፈውሰው አላየውም። *እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም።* ቁ. 38። ይህ ያላመነ ሰው እንኳ ተፈወሰ።

የፈውስ ስጦታ አለኝ ያለ ሰው እኮ ያ ፈውስ የፈውስ ስጦታ ነው እያለ ወይም እያረጋገጠ ነው ያለው። ስጦታ በተግባር ይታያል። የመስጠት ስጦታ ያለው ሰው ይሰጣል። የማስተማር ጸጋ ያለው ሰው ያስተምራል። የመስበክ ስጦታ ያለው ይሰብካል። የመፈወስ ስጦታ ያለውስ? ግልጽ ነው፤ ይፈውሳል። ‘ስላላመነ ነው ያልተፈወሰው’ የሚሏትን ዘፈን የሚዘፍኑልን ሰዎች አጭበርባሪ ስለሆኑ ብቻ ነው። ወይም ቃሉን ፈትሸው የሚጠይቁ ሰዎች እንደሌሉ ስለሚገምቱ ብቻ ነው።

## የተአምራትና የፈውሶች ክምችት ዘመናት

እግዚአብሔር ፈውስንና ተአምራትን እንደ ሻሞ ዕቃ አይረጭም፤ አይበትንም። ተአምር ተሠርቶ ትራፊውን እንኳ እንዲሰበስቡ አድርጎአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የተአምራትና ፈውሶች አንጓ ወይም ክምችት ዘመናት አሉ። ሦስት ዘመናት ናቸው። እነዚህ ዘመናት ከነዚህ ተአምራት ከተደረጉባቸው ሰዎች ጋር የተቆራኙ ናቸው። አንድና ሁለት ብቻ ሳይሆን በተደጋጋሚ በርካታ ተአምራትና ምልክቶች በሰዎቹ አማካይነት የተደረጉባቸው ናቸው።

1ኛ፥ የመጀመሪያው የሙሴና ኢያሱ ዘመን ነው። ሰዎቹም ሙሴና ኢያሱ ናቸው። በነዚህ በሁለቱ እጅና በዘመናቸው አንድና ሁለት ሳይሆን ብዙ ተአምራት ተደርገዋል። እነርሱ ባሉበት ተአምራት ሆነዋል፤ ባሕር ተከፈለ፤ ወንዝ ተከፈለ፤ መና በሉ፤ በጦርነት ድል ነሱ፤ ውኃ ደም ሆነ፤ መሬት ተከፈለች፤ ወዘተ።

2ኛው የተአምራት ክምችት የምናገኝበት ዘመን የኤልያስና ኤልሳዕ ዘመን ነው። ሰማይ ተዘጋ፥ ተከፈተ፤ እሳት ከሰማይ ወረደ፤ ዘይት በዛ፤ ብረት ተንሳፈፈ፤ ወዘተ። ኤልያስ እና ኤልሳዕ በነበሩበት ዘመናቸው ሁሉ፥ ባሉባቸው ቦታዎች ሁሉ፥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተአምራት ኖሩ። አስፈላጊ ሲሆን የሚለው ይሰመርበት። ተአምር ለትርዒት፥ ለትዕይንት አይደረግም። ‘ይሄንን እግር ላስረዝም?’ እየተባለ ፌዘኞቹ ኢዩ ጩፋ፥ ሀብታሙ ይዲድያ፥ ፊልጶስ ሲራንዮና እነ ቡሺሪ እንዳደረጉት የመሰለ ድራማ ለማሳየት ተአምር አይደረግም፤ ያ ተአምር ሳይሆን ጥሬ ማጭበርበር ነው። ያውም ጥሬ፥ ያልበሰለ፥ ያልሰለጠነ ማጭበርበር። ቁመት ማርዘም አስፈላጊ አይደለማ! ለዓይን ግን ይስባል፤ ለማታለል ግን ይመቻል። የነኤልያስና ኤልሳዕ ዘመን ማታለልን አያውቃትም። ሁለተኛው የክምችት ዘመን ያ ነው።

3ኛው የፈውስና የተአምራት ክምችት ዘመን የጌታና የሐዋርያቱ ዘመን ነው። ጌታ በተገኘበት ፈውስና ተአምር ሲያስፈልግ አለ። ወንጌላቱ የዚህ ምስክር ናቸው።

ድውያን ተፈውሰዋል፤ ሙታንም ተነሥተዋል። ጌታ እርሱ ጌታ ነውና ፈውስና ተአምራት ገንዘቦቹ ናቸው። አሁንም ሲያስፈልግ የሚለው ይሰመርበት። ለታይታና ለእይታ፥ ለአድናቆትና ለማስደነቅ የተደረጉ ነገሮች የሉም። በሐዋርያቱ ዘመንም እንዲሁ። ከሐዋርያቱ ፈለጋቸውን በመከተል የአገልግሎት ታሪካቸው የተጻፈልን ከመጀመሪያዎቹ ከ12ቱ የአንዱ የጴጥሮስ፥ ከኋለኞቹም የአንዱ የጳውሎስ ብቻ ነው። የሌሎቹም አልተጻፈም እንጂ ተአምራትና ፈውሶች መኖራቸውን በቀላሉ መገመት እንችላለን። በሁለቱ በጴጥሮስና በጳውሎስ እጆች ፈውሶችና ተአምራት ተከትለዋቸዋል። የታመሙ ተፈውሰዋል፤ በሁለቱም እጅ የሞቱም ተነሥተዋል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ማስተዋል ያለብን ፈውስና ተአምራቱ በጌታ ፈቃድ የተደረጉ እንጂ በሰዎቹ ፈቃድ አልሆኑም።

## የፈውስና ተአምራት ስጦታዎች ተቋርጠዋል?

ሦስቱ የተአምራት ከምችቶች አንጓዎች ዘመናት እነዚህ ከላይ ያየናቸው ናቸው። በሦስተኛው አንጓና ከምችት ዘመን ገና በእነርሱ ዘመንም እንኳ ተአምራቱም ፈውሶቹም እየሳሱና እየቀሩ መጡ። ታመው መድኃኒት የታዘዘላቸውና ሳይፈወሱ የቀሩም ተጽፈውልናል። ራሱ ጳውሎስም እንኳ የሥጋው መውጊያ የሆነ ሕመም ነበረበት። የጸጋ ስጦታዎች፥ በተለይም የተአምራትና የፈውስ ስጦታዎች ቀርተዋል ወይም ተቋርጠዋል የሚሉ ሰዎች ይህንን የሚሉት ለምን እንደሆነ መገመት እንችላለን። ከሚሉባቸው ምክንያቶች ዋናዎቹ ሁለት ናቸው፤

<u>አንደኛው፥ የቀድሞው ዘመን ምክንያት የሚባለው ነው።</u> ራሱ የፈውስና የተአምራት ምልክቶች በራሳቸው በሐዋርያቱ ዘመንም መጨረሻ እንኳ መቅረታቸው ወይም መቋረጣቸውና ከራሳቸው ከሐዋርያቱና አብረዋቸው ከሚያገለግሉት መካከል አንዳንዶቹ ታመው ሳይፈወሱና ከሞት ሳያመልጡ መቅረታቸው ነው።

<u>ሁለተኛው፥ የዛሬ ዘመን ምክንያት ነው።</u> ዛሬ ‘ፈውስ’ የሚባሉት ነገሮች የውሸት ሆነው ሲገኙና፥ ‘ተፈውሳችኋል’ የተባሉት ሰዎችም ሳይፈወሱ ሲቀሩና ሲሞቱ መገኘታቸው ነው።

የፈውስ ስጦታ መቋረጥን ወይም መቀጠልን በተመለከተ ልብ ማለት ያለብን ሁለት ነገሮች አሉ።

1ኛ፥ የፈውስ ስጦታ አለን የሚሉ እውነተኛ ሰዎች ከኖሩ እውነተኛ ፈውስ ልክ እንደ ክምችቶቹ ዘመናት እነዚህ ሰዎች በየሄዱበት መኖር አለባቸው። ታመው መጥተው ሳይፈወሱ የሚመለሱ መኖር የለባቸውም። ሲያስፈልግ ወደ ሆስፒታሎችም ብቅ እያሉ ሕሙማንን እና ድውያንን ሲፈውሱ ማየት አለብን። ስጦታ ነዋ! ሰባኪ በቤተ ክርስቲያንም በመንገድም ይሰብካል፤ ስጦታው ስለሆነ። ፈዋሽም ያንን እንዲያደርግ ብንጠብቅ ለምን ያስደነግጣል? እንደዚህ የሚያደርጉ ካልኖሩ ተቋርጧል የሚሉ ሰዎች መኖርም ማስደንገጥ የለበትም።

2ኛ፥ ተቋርጧል የሚሉ ሰዎች ስጦታው ነው ተቋርጧል የሚሉት እንጂ የእግዚአብሔር የፈውስና የተአምር አድራጊነት ሥልጣን አይደለም የተቋረጠው። እግዚአብሔር ዛሬም ይፈውሳል። በሰው ወይም ያለ ሰው ይፈውሳል። በሽማግሌዎች ዘይት መቀባት ወይም በማንም አማኝ ምልጃ አማካይነት ሊፈውስ ይችላል፤ ከወደደ። 'ከወደደ' የሚለው ይሰመርበት። ከፈቀደ። እግዚአብሔር ከፈቀደ በምንምና በማንም ብቻ ሳይሆን ያለ ምንም እና ያለ ማንም ይፈውሳል። ፈውስ ፈውስ መጫወት እየበዛ ሲመጣ መጠየቅ የግድ ይሆናል።

## ከወደደና ከፈቀደ ብቻ

'ከወደደ፥ ከፈቀደ' ሲባል፥ 'እንዴት አይወድድም? እንዴት አይፈቅድም? እንዴት ሰዎች ሲታመሙ መፈወስ ፈቃዱ አይሆንም?' የሚሉ ደፋሮች አሉ። እግዚአብሔርን እኛ እንዴት ነው፥ 'እንዴት አይፈቅድም?' የምንለው? እኛ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ አዛዦች ስንሆን አይታችሁታል? በእርሱ ፈቃድ ላይ እኛ ባለ ሥልጣን የምንሆነው፥ የምንሠለጥነው ከምንነታችን የተነሣ ነው? ምን ከመሆናችን፥ ማን ከመሆናችን የተነሣ? እጁን የምንከለክል ወይም እጁን አዝዘን የምናሠራት እኛ ማን ነን? የብዙ ፈውሰኞች እና 'የብልጽግናና የጤንነት ወንጌል' የሚባለው ልዩ ወንጌልና ሽፋፋ ወንጌል ሰባኪዎች ስሕተት ይህ ነው። እግዚአብሔር ጌታቸው ሳይሆን አገልጋያቸው ነው። እግዚአብሔር ማለት እነሱ የሚፈልጉትን ፍላጎታቸውንና ምኞታቸውን እንደ ሎሌ ታጥቆ የሚያገለግል አገልጋይና አሽከር ነው።

እንደ ቃል እምነትና የብልጽግናና የጤንነት ልዩ ወንጌል አስተማሪዎች፥ እኛ እገሌ እንዲፈወስ ፈቃዳችን ከሆነ፥ እግዚአብሔር በግድ ማድረግ አለበት። ይህ የኛ ፈቃድ የእግዚአብሔርም ፈቃድ እንደሆነ ይታሰብና፥ እኛ የእርሱ ፈቃድ በሕይወታችን ትሁን ማለት ሳይሆን የኛ ፈቃድ የርሱ ፈቃድ ናት ብለን፥ እርሱን የኛ ፈቃድ አገልጋይ እናደርገዋለን። እግዚአብሔር የሚታዘዝ አገልጋይ ነው እኮ! እውነቱ ግን የዚህ ተቃራኒ

ነው። እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ፈቃዱን ያደርጋል፤ *በምድርም የሚኖሩ ሁሉ እንደ ምናምን ይቈጠራሉ፤ በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ እጁንም የሚከለክላት ወይም፡- ምን ታደርጋለህ? የሚለው የለም።* ዳን. 4፥35።

የእርሱ ፈቃድ ዋናዋ ናት፥ ትልቂቱ! ፈውስ በዚህ ዘመን ከኖረ እንደ ፈቃዱ የሚሆን እንጂ፥ እንደ ማብሪያና ማጥፊያ ብልጭ ድርግም የምናደርገው ነገር አይደለም። ቢሆንማ ፈውሰኞች አድራሻቸው የት መሆን ነበረበት? ሕሙማንና ድውያን በሚገኙበት።

## ይጠየቃል!

ፈውስ አለ ከተባለ ይጠየቃል። መኖሩ ይፈተሻል፤ ይረጋገጣል፤ ካልኖረ ደጋግሜ እንደምለው፥ ፈውሰኛው፥ 'ቀጣፊና አጭበርባሪ፥ አምታችና አሳች' ይባላል። ፈውስ ይጠየቃል፤ ተአምር ይፈተሻል። መጠየቅ ነውር አይደለም። መፈተሽ ክህደት አይደለም። ፈውሰኛን መጠራጠር ጌታን መካድ አይደለም። ጴንጤቆስጤው ማኅበረ ሰብ፥ በተለይም የአገራችን ጴንጤቆስጤው ማኅበረ ሰብ የአጭበርባሪና ምናምንቴ ዱርዬዎች መጫወቻ ለመሆን በራሱ ላይ የፈረደ ሕዝብ ነው። የቀረበለትን ሸቀጥ ሁሉ ሳይጠይቅ፥ ሳይፈትሽ፥ በጅምላ ዋጋ ሳይሆን በችርቻሮና በማጣሪያ ዋጋ ይገዛል። የተበላሸ ስለሆነ ሊመለስ ቢሞከር አይሠራም። ሳይጠይቅ ብቻ ሳይሆን ያለ ደረሰኝ ነው የሚገዛውና የተበላሸ ዕቃ እንደሚመለስ አይመለስለትም። የተበላሸ ተአምር አይመለስም። የተበላሸ ፈውስ አይመለስም። የተበላሸ ተስፋ አይመለስም። የተበላሸ ትንቢት አይመለስም። አይመለስም! ከተመለሰ ማን ይገዛል? እዚያ ሱቅ፥ እዚያ መደብር ማን ይሄዳል? ስለዚህ እያመመህ፥ እያለቀስክ ትከፍላለህ፤ ትከስራለህ።

ስለዚህ ይጠየቃል። እውነት ፈውሱ አለ? ፈውሱ እውነተኛ ነው? ተብሎ ይጠየቃል። እውነተኛ ከሆነ ጌታ ይመሰገናል። ፈዋሹ ጌታ ነዋ! ሰውየው፥ 'የለም፤ እኔ ነኝ!' ካለም፥ እንዲያውም ለመጠየቅ ፈቀደ ማለት ነው። ፈውሱ ውሸተኛ ከሆነም አሁንም ሰውየው፥ ማለትም ፈውሰኛው ይጠየቃል። ለምን?

1ኛ፥ በመጀመሪያ፥ 'የፈውስ ስጦታ አለኝ' ያለው እርሱ ነው። ማስታወቂያ የለጠፈው፥ ያስለጠፈው፥ ስለ ራሱ የተናገረው፥ ያወጀው፥ ያሳወጀው እርሱ ነው። ያ ጸጋ፥ ያ ስጦታ ከሌለው፥ 'የለኝም' ማለት ይችል ነበር። አላለም። የሌለውን፥ 'የለኝም' እያለ ሌሎች፥ 'አለህ እንጂ!' አላሉም። 'ጌታ በዚህ ጊዜ፥ በዚያ ቦታ ድንቅና ተአምር አድርጎ!'

እያለ መጀመሪያ ያስወራው እርሱ ራሱ ነው። ሰው ተግተልትሎ እንዲወጣ ያደረገው እርሱ ነው። ሌሎች ሲናገሩም አልተከላከለም፤ ማስተባበል ሲችል አላስተባበለም። ስለዚህ ስለ ራሱ የተናገረ እርሱ ራሱ ነውና ይጠየቃል።

2ኛ፥ ‘ተፈውሰሃል፤ ተፈውሰሻል’ ያለው እርሱ ነው። እርሱ ስል በተለምዶ በወንድ ፆታ አልኩ እንጂ እርሷ ሊባልም ይቻላል። ተፈውሰሃል ያለው፥ ‘ቃል’ ያወጣው እርሱ ነው። ውኃ የረጨው፥ ዘይት የቀባው እርሱ ነው። የሸጠውም የቸረቸረውም እርሱ ነው።

3ኛ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈውስ በተደረገበት፥ ፈውስ ባለበት ቦታ ሁሉ ውሸታም ፈውስ ፈጽሞ አልታየም። ያላመኑ ሰዎች እንኳ ተፈውሰዋል። ንዕማን ከለምጹ ሲፈወስ ፈውስ ነው። የፑፕልዮስ አባት ከንዳድና ተቅማጥ ሲፈወስ የእውነት ፈውስ ነው። ይህን አይተው ብዙ የዴሴቱ ሰዎች እየመጡ ተፈወሱ። ይህ የጳውሎስ የተመዘገበልን የመጨረሻው የፈውስ አገልግሎት ነበር። የጴጥሮስ አማት ከንዳድ መፈወሷ ፈውስ ነው። ተፈውሳ፥ ተነሥታም አገለገለቻቸው። ፈውሶች በተጻፉባቸው ቦታዎች ሁሉ ፈውሶቹ ምንም የማያጠያይቁ እውነተኛ ፈውሶች ናቸው። ውሸታም ፈውስ ከኖረ በጣም መጠየቅ ያለብን ከቃሉ ጋር ስለሚጋጭ ነው።

ስለዚህ ይጠየቃል፤ በአገራችን ጴንጤቆስጤው ማኅበረ ሰብ ዘንድ እንዲህ የመሰሉ ጥያቄዎች መጠየቅ እንደ ነውር፥ እንደ አላማኒነት፥ እንዲያውም እንደ ከሀዲነት፥ በመንፈስ ቅዱስ እንዳለማመን፥ (መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ በእግዚአብሔር እንዳለማመን ስለሚቆጠር፥ እንደ ነውር ተደርጎም ስለተስተማረ፥ እንዳይጠየቅም ብዙ ስለተነገረ፥ ተርታው ሕዝብ ቃሉንም ስለማያውቅና ስለማያነብብ፥ የውሸት ፈውስ እየታየም እንኳ አይጠየቅም። ሰዎች ሳይፈወሱ ሲቀሩ፥ ሕመሙ ሲብስባቸውና ሲበረታባቸው፥ ሲሞቱም እንኳ አይጠየቅም። መጠየቅ ነውር ነው። ጴንጤቆስጤው ማኅበረ ሰብ ስል እንደ ሙሉ ወንጌል ያሉትን ፔንቲኮስታል እብያተ እምነቶች ብቻ ሳይሆን እንደ ቃለ ሕይወት ያሉትንም፥ በአባልነት ቃለ ሕይወት በልምምድ ጴንጤቆስጤ የሆኑትን ማለቴ ነው። እነዚህ ከቃሉም ከአመክንዮም ጋር የተፋቱ ስለሆኑ አይጠይቁም። ግን ይጠየቃል።

## ስደመድም

ፈውስ አለ? አዎን አለ። የፈውስና ተአምራት ስጦታዎች ተቋርጠዋል? የትኛውም ስጦታ አልተቋረጠም። እንደ ቅዱስ ቃሉ ከተደረገ አለ። ፈዋሽ ማን ነው?

እግዚአብሔር። ማንም ስምና ዝና አይወስድም። ፈውስ አለ? አዎን አለ? እንዴት? እንደ ጌታ ፈቃድ። እርሱ ከፈቀደ ብቻ ይሆናል።

‘ስላላመኑ ነው!’ የሚሏት ዘፈንስ? እርሷ የአጭበርባሪዎች ዘፈን ናት፤ እንዳይጠየቁ ሰብረው የሚያልፉባት ኬላ ናት። ያመኑም ተፈውሰዋል፤ ስላላመኑ ሳይፈወሱ የቀሩ ሰዎች ግን አልነበሩም።

የተአምራትና ፈውሶች ክምችት ዘመናት በቃሉ ታሪክ ውስጥ ታይተዋል። ዛሬ እንደዚያ ያሉ ሰዎች፥ በሄዱበት ሁሉ ተአምርና ፈውስ ልክ እንደ ጥላቸው ተከትሎአቸው የሚሄድ ሰዎች አሉ? የሉም። ሆስፒታል ሲሄዱ ድውያን ሁሉ ከአልጋ ተነሥተው የሚሄዱበት፥ በሬሳ አጠገብ ሲያልፉ ሙታን የሚነሡበት ዓይነት ሰዎች የሉም። ፈውስ ግን እንደ ጌታ ፈቃድ አለ።

የውሸት ፈውስስ አለ? ምን ጥያቄ አለው? አለ እንጂ! ያኔ ምን ይደረጋል? ይጠየቃል፤ ይፈተሻል፤ ይመረመራል፤ ይበረበራል። ፈውሰኞቹ ውሸታሞች ሆነው ሲገኙ ይገለጣሉ፤ ንስሐ እንዲገቡ ይጠየቃሉ፤ የማይገቡ ከሆኑ ከአገልግሎት ይወገዳሉ፤ ለሌሎችም አጭበርባሪዎች መሆናቸው ይነገራል።

# የፈውስ ስጦታ እና የፈውስ ቀውስ (ከመቅካቀ መጽሐፍ)

እነዚህ ሁለት ክፍሎች የተወሰዱት ከመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፌ ነው። የፈውስ ስጦታዎች ከገጽ 83-83፤ የፈውስ ቀውስ ደግሞ ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 212-225 እንዳለ የተወሰዱ ናቸው።

## የፈውስ ስጦታዎች

'ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ. . .' (1ቆሮ.12፥9) ይህ ስጦታ በተጠቀሰባቸው ቦታዎች 'ስጦታ' ተብሎ በነጠላ ሳይሆን 'ስጦታዎች' ተብሎ ነው በብዜት የተነገረው። ምናልባት በሽታዎች ሥጋንና ነፍስንም የሚነኩ ስለሆነ ሊሆን ይችላል። ይህ ስጦታ እግዚብሔር ሰዎችን ከሥጋዊ፥ አዕምሯዊና ስሜታዊ ደዌና ጭንቀት በማያዳግም ሁኔታ የሚፈውስበት ስጦታ ነው። ይህም ሰዎቹ ፍጹም ጤናማ የሚሆኑበትና አማኞች ደግሞ የሚታነጹበት ለማያምኑ የእግዚአብሔር ኀልውናም ምልክት የሚሆንበትና እግዚአብሔርም የሚከብርበት ነገር ነው።

ፈውስ በሁለት መንገዶች እንደሚደረግ አዲስ ኪዳን ይነግረናል። የመጀመሪያው በሽተኞች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ይጠሩና ሽማግሌዎችም ዘይት ቀብተው የሚጸልዩላቸው ወይም ምዕመናንም እጆቻቸውን በመጫን የሚጸልዩበት አገልግሎት ነው። (ያዕ.5፥14 እና ማር. 16፥18) በዚህ ጸሎት ላይ እምነት ሊታከልበት እንደሚገባ ግልጽ ሆኖ ተነግሯል። ሁለተኛው ደግሞ የፈውስ ስጦታ በተሰጣቸው ምዕመናን አማካይነት የሚደረገው ነው። እነዚህ አገልጋዮች በአገልግሎታቸው መቼ የትና እንዴት መሰማራት እንዳለባቸው በመጸለይ የጌታን ፈቃድ ማወቅ እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ጋር በመነጋገርና በመጸለይ ለታመሙ የሚጸለይበት አገልግሎት ነው።

ሕመም ስንል አካልንና አዕምሮን የሚጎዳ ስቃይ ማለታችን ነው። ጌታ ብዙ ድውያንን ፈውሶ ነበር። የአንዳንዶቹ ሕሙማን ሕመማቸው ምን መሆኑ አልተጠቀሰም። ከተጠቀሱት መካከል ግን ሽባ፥ አንካሳ፥ለምጽ፥ዕውር፥ ዲዳና ደንቆሮ፥ የሚጥል በሽታ፥

ንዳድ፥ የደም መፍሰስ ይገኙባቸዋል። ጌታ መጀመሪያ 12ቱን በኋላም 72ቱን ሲልካቸው (ሉቃ.9 እና 10) ድዊያንንም ይፈውሱ ዘንድ ስልጣን ሰጥቷቸው ነበር። በሐዋርያትም የፈውስ ምልክቶች ተደርገው ነበር፤ ለምሳሌ፥ አንካሳ ተፈወሰ (ሐዋ.3) ሽባ ተነሣ፤ (ሐዋ.9) ከተወለደ ጀምሮ ሄዶ የማያውቅ አንካሳም ተፈውሶ ተመላለሰ። (ሐዋ.14) እግዚአብሔር በባሕርዩም ፈዋሽ አምላክ ነው፡ (ዘጸ. 15፥26) ስለዚህም ይፈውሳል። ይህ ማለት ግን መፈወስ ግዴታው ነው ማለት አይደለም። የፈውስ አገልግሎት ሲወሳ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ወደጎን መደረግና መዘንጋት የለበትም። ከዘመናችንም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታምመውና ተጸልዮላቸው ያልተፈወሱ ቅዱሳንን ስናስብ ይህንንም አብረን ማጤን ይገባናል።

በዚህ ዘመን የዚህ ስጦታ መኖር እውነት ነው። የዚያኑ ያህል ሰዎች ሲያበላሹትና ያልተሰጣቸውም እየኮረጁ ሲለማመዱት ስለሚታይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። አገልጋዮና ታማሚው ሲገናኙ አገልጋዮ ስጦታው እንዳለው ታማሚውም በሽታው እንዳለበት ታማኝ ሆነው መነጋገር አለባቸው። በተለይ አገልጋዮ የፍቅር ስሜት ሊኖረው ይገባል። ይህ ደግሞ ስሜታዊ በመሆን የሌለ ፈውስን እንዳለ መቁጠርና ያልተፈወሰ ሕመምን ደግሞ እንደሌለ መቁጠር አይደለም። የፈውስ ስጦታ ከኖረ ፈውስም አለ ማለት ነው። የተጸለየለትም ሰው ያልተፈወሰ እንደሆነ ሊፈረድበትና ሊኮነን አይገባውም። እምነት-ጎዶሎም ተደርጎ መንኳሰስ የለበትም። በሽተኛው ካልተፈወሰ ተጠያቂነቱ በአመዛኙ መውደቅ የሚገባው በስጦታው እውነተኛነት ላይ ነው። ከዚህም ባሻገር የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንነት መስተዋል አለበት። ስጦታው የሌላቸው አገልጋዮች ለሕሙማን ይጸልዩና ሕመምተኞቹ ካለተፈወሱ አነዚህ አገልጋዮች ራሳቸውን እውነተኛነት ከመመርምር ይልቅ የበሽተኞቹን እምነት መመርምር ይቀናቸዋል። በሽተኞቹም ያለመፈወሳቸው ሳያንሳቸው የእምነታቸውን ቁርቁዝና (እምነተ ቢስነታቸውን) ተሸክመው ይመለሳሉ። የነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ቢጎዳ እንግዲህ አያስገርምም። ለዚህ ነው ጥንቃቄ የሚያሻው።

አንዳንዴ በጉባኤ መሟሟቅና የስሜት ግለት ሕሙማን እውነተኘነት የሌለው የፈውስ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ያንንም ስሜት 'ፈውስ' ነው ብለው 'በእምነት' ለመቀበል መገደድ የለባቸውም። እውነተኛ ፈውስና ውሸታም ስሜት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ፈውስ ከኖረ ለሕመምተኛው ብቻ ሳይሆን ለተመልካችም ጭምር ሊታወቅ ይችላል። የፈውስ ስጦታ ያላቸው አማኞች በሌሎች ዘንድ እንደ ልዩ ተአምር አድራጊዎች ወይም ደግሞ እንደ ምትሃተኞች ሊታዩ ስለሚችሉ በአገልግሎታቸው ወቅትም ሆነ ከዚያ ውጪ ሰዎችን አትኩረት እንዳይስቡ መጠንቀቅ አለባቸው።

‘ተፈውሰሃል!’ ‘ተፈውሰሻል!’ ሲባል ይጠየቃል። ዘ. መ.

## የፈውስ ቀውስ

ከሁለት ዓመታት በፊት ቤኒ ሂን ሲያካሂድ በነበረው የ ‘ፈውስ’ እና ‘‘በመንፈስ መሰየፍ’’ (slaying in the Spirit) ‘አገልግሎት’ ወቅት አንዲት ወፍራም ሴት በአንዲት አሮጊት ላይ በመገንደሷ የአሮጌቷም የዳሌ አጥንት በመሰበሩ የ5 ሚሊዮን ዶላር ካሳ እንዲከፍል ተጠይቆ ነበር።

በ1988 ዓ.ም. ደግሞ በመቱ ከተማ ታላቅ የፈውስ ጉባኤ እንደሚደረግ የሚናገሩ ማስታወቂያዎች እየተለጠፉ ብዙ የበሽታ ዓይነቶች እየተጠሩ ድውያን ወደ ጉባኤው ቦታ ታደሙ። ጉባኤው የተካሄደው ለሦስት ቀናት ሲሆን ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ውጤቱን ብቻ ልናገር፤ በነዚህ ሦስት ቀናት ውስጥ በዓይን ከሚታይና በአካል ከሚታወቅ በሽታ የተፈወሰ አንድም ሰው አልነበረም። በሁለተኛው ቀን ደግሞ የሚዘገንን ታሪክ ተፈጸም። ፈውስ ፍለጋ ወደ መድረክ የሄደች የልብ ድካም የነበረባት ሴት እመድረክ ላይ ወድቃ ቆይታ ሞታ በዕለቱ ማብቂያ ላይ ከአዳራሹ ሬሳዋ ወጣ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያውም በምዕመናን መካከል ለሚፈጸሙ ይህን መሳይ አሳፋሪ ነገሮች ቃሉም መሪዎችም የዝኖን ጆሮና የዓሣ አንደበት ይስጠኝ ሊሉ አይገባም።

በዚህ ዘመን ሕመምን፥ ፈውስንና ጤንነትንም በተመለከተ የተቃወሰ አመለካከት አለ። ይህ አመለካከት በጥቅሉ ‘‘አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን የክርስቶስ አካል ሆኗልና ማናቸውም ዓይነት ሥጋዊ መከራና በሽታ ሊነካው አይችልም፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለክርስቲያን የተሟላ ጤንነትና ቅጽበታዊ ፈውስ ነው። ጤንነት የጤናማ ክርስትና ሕመም ደግሞ የበሽተኛ ክርስትና ምልክቶች ናቸው’’ የሚል ነው።

እንዲህ ያለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ራሳቸው አይታመሙም ማለት አይደለም። እየታመሙ ብዙ ያሳለፉ አሉ። ክርስቲያን መታመም የለበትም የሚሉ ሰዎችን ሲታመሙ ሁለት መጥፎ ነገሮች ይጋፈጧቸዋል። የመጀመሪያው ያንን ሕመም ስለማይጠብቁት እንዴት አድርገው እንደሚስተናግዱት ግር ይላቸዋል። ሁለተኛውና ከዚያኛውም የባሰው ደግሞ በሽታውን አይቀበሉትም እያሳመማቸው እንደሌለ ይቆጥሩታል፤ ይክዱታል። እያደር የሚጠና መጥፎ በሽታ ምልክት እንኳ ቢሆን ‘ውሸት ነው’ ይሉታል እንጂ መከላከያ ሊወስዱ አይቃጣቸውም። መድኃኒት መውሰድ ደግሞ መፍራት ሲሆን ፍርሃት ደግሞ በተራው በሽታውን የማሳደጊያ ቀለብ ነው ብለው ይገምታሉ። በሽታው ስለተካደ የለም ማለት አይደለም። ‘ክርስቲያን ሳይንስ’ የሚባለውና ሌሎችም መሰል ዲበ አካላዊ (metaphysical) የስሕተት ትምህርቶች ሕመምን እውን እንዳልሆነ እንደ አንድ ዓይነት ቅዠት ይቆጥሩታል።

ሰው መጀመሪያ ለምንም ዓይነት ጉስቁልና አልነበረም የተፈጠረው። ሊሞትም አልነበረም። መርገም የመጣው ከሰው ኃጢአትና ውድቀት በኋላ ነው። ሕመምና ስቃይም የዚህ ፍርድ ቅርንጫፎች መሆናቸው ግልጽ ነው። እነዚህ ነገሮች ማንንም አይመርጡም፥ ማንንም አይለዩም። አንዳንድ ተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ቢከሰቱ እነዚህ ነገሮች ሆን ብለው ክርስቲያን ያልሆኑትን ብቻ እየመረጡ ያጠቃሉ ማለት አይደለም። እዚህ ላይ መካድ የሌለበትም ሐቅ አለ፤ ያም እግዚአብሔር ጠባቂ አምልክ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር መቅሰፍትን በግብጽ ላይ ሲልክ ጌሴምንና በውስጧ የነበሩትን እስራኤል ሁሉ ጠብቆ ነበር። ግብፅን ለቀው ከመውጣታቸው በፊትም አጥፊው መልአክ በመቃኑና በጉበኖቹ ደሙ ያለበትን በር እያለፈ ይሄድና ባልተቀባበት ቤት እየገባ በኩሩን ይገድል ነበር። ጌታ ሕዝቡን እንደሚጠብቅም ብዙ ተስፋ ሰጥቷል።

የእግዚአብሔርን ጠባቂነት ስናስብ ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወታችን የወደደውን ቢያደርግ ማንም የማይጠይቀውና የማይቆጣው አምልክ የመሆኑንም እውነት ማለፍ የለብንም። ሲያጠፉ ይቀጣል፥ መልካም መስሎ ከታየው ደግሞ ባያጠፉም ለመጠበቅና ለማስተማር ወይም እኛ ለማናውቀው ወይም ልናውቀው ለማንችለው ምክንያት እኛ የማንወደውን ቅጣት የሚመስልን ነገር ወደ ሕይወታችን ሊያመጣ ይችላል። በርግጥ እንደ ጥፋታችን የማይቀጣን አምላክ ቢሆንም አጥፍተን ከሆነና ካወቅነው ልንታረም ካልሆነም በአባታዊ ፍቅሩ ታምነን ልንታገሰው ይገባናል። ስለ ቅጣት ስናስብ ከግብፅ ከወጡት እስራኤል የሚበዙቱ በምድረ በዳ ወድቀው መቅረታቸው ምሳሌ ሊሆንልን ይችላል። ሳያጠፉ ፍዳን ለተቀበሉት ኢዮብን፥ ለታመሙትም ጳውሎስን ጢሞቴዎስንና ሌሎችንም እንደ ምሳሌ ልንወስድ እንችላለን።

የዚህ ‘ክርስቲያን መታመም የለበትም ’ የሚለው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነጥብ የሚነሣው ከኢሳ.53፥4-5 እና ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሰባቸው ሁለት ቦታዎች ማለትም ከማቴ.8፥16-17 እና 1ጴጥ.2፥22-25 ነው። ዋናው ትምህርቱ አሳብም ክረስቶስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል በሽታችንንም ሁሉ ነው የተሸከመልን እና ከመስቀሉ ወዲህ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በበሽታ መነካት የለባቸውም የሚል ነው። እንደነዚህ ሰዎች ትምህርት ሥጋዊ ሕመም የመንፈሳዊ ችግር (የውስጣዊ/መንፈሳዊ በሽታ) ውጪያዊና አካላዊ ምልክት ሲሆን ከመንፈሳዊ ሕይወት ያለመስተካከል የሚመጣ ነው። በተጨማሪም የሰው አሉታዊ ንግግር (Negative Confession) በሽታን ያመጣል። በአሳብም ይሁን በቃል በሽታ በአካላችን እንዳለ ስናስብና ስንናገር ሰይጣን ዕድል ያገኝና ይወርረናል በሽታም ይይዘናል ይላሉ።

> የእምነት አስተማሪዎቸች ደጋግመው ይህን መሳይ ማስጠንቀቂያ ለጉባኤያቸው ይናገራሉ። በጣም አክራሪ በሆኑት (የዚህ) እምነት አብያተ ክርስቲናት ደግሞ አንድ ክርስቲያን የጸሎት ጥያቄ ለማቅረብ እንኳን በሽታን መጥራት የለበትም። እንዲህ ያደረጉ ከኖሩ ይገሰጹና ‘ቃሉን እንዲናገሩ’ (የጌታን ቃል ማለት ነው) እና ስለተፈወሱ እንዲያመሰግኑ ይነገራቸዋ።[33]

ከዚህ መጠቅ ያለውን የሚያስተምሩት ደግሞ አንድ ክርስቲያን ከ70-120 ዓመት ሳይሞላው መሞት እንደሌለበት ያስተምራሉ። ከነዚህ የባሱት ሌሎች ደግሞ (ለምሳሌ፥ ‘የተገለጡት የእግዚአብሔር ልጆች’ የሚባለው ማኅበር) አንድ ክርስቲያን እንደነ ሄኖክና ኤልያስ መነጠቅ አለበት እንጂ ጭራሽ መሞትም እንደሌለበት ይናገራሉ።

ከላይ ባየናቸው ሦስት ምዕራፎች (ኢሳ. 53፥ማቴ.8 እና 1ጴጥ.2) ፈውስ የሚለው ቃል ተጽፏል። መጀመሪያ የተጻፈው በኢሳይያስ ‘ሆኖ’ ማቴዎስና ጴጥሮስ ያንን ነው የጠቀሱት። በኢሳይያስ የተጠቀሰው የቃሉ ትርጉም (በዕብራይስጥ ‘ራፉ’ የሚባለው) መፈወስ፥ መዳን፥ደህና መሆን፥ ጤናማ መሆን እንደማለት ነው። ቃሉ በብሉይ ኪዳን ሰፋ ተደርጎ ተጠቅሷል። ሁሌም የሥጋ ፈውስን ብቻ አይናገርም፤ ለምሳሌ፥፥

መሻር፤ (ቁስል፥ ቤት ወዘተ.) ዘሌ.13፥18-37፤14፥48‘

መጥፋት (የለምጽ)፤ ዘሌ.14፥3

መፈወስ (ውኃ፥ ሰው፥ከተማ፥ ባሕር ወዘተ.) 2ነገ.2፥22፤ኢሳ.53፥5፤ ኤር. 3፥22፤17፥14፤51፥8-9፤ሕዝ.47፥8-9

ኢሳ. 53ን በሙሉ ስናነብበው የመሢሑን ስቃይ እናያለን። የመሢሑ ሥጋ መልበስ ዋና ዓላማ ደግሞ ከኢሳ. 53 ብቻ ሳይሆን ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ኃጢአታችንን ተሸክሞ ሊሞትና በሞቱም እኛን ሊያድን ነው። ይህ ደኅንነት ነው፤ ይህ መዳን ነው። ጌታ መሸከም የነበረበት ዕዳ እኛ መሸከም የነበረብን ነበር። የሕማም ሰውና ደዌን የሚውቀው ጌታ ይህን የሆነው ለኛ ሲል እኛ ማለፍ የነበረብንን ግን ልናልፈው ያልቻልነውን የደኅንነት ጎዳና ለመሄድ ነበር።

ኢሳ. 53፥2-4ን የወሰድን እንደሆነ ስለ ራሱ ስለ መሢሕ ሥጋና ስለ ሥጋዊ ፈውስም ይናገራል። ጌታ ፈዋሽ መሆኑ በወንጌላት በግልጽ የተጻፈ እውነት ነው። ነገር ግን መሢህ የቆሰለው ስለ መተላለፋችን የደቀቀውም ስለ በደላችን ነው። ይህ ነው የመሲሑ ሥጋ መልበስ ዋና ዓላማ፤ እንጂ ጌታ ሥጋን የነሣው በሽታችንን በመስቀል ላይ ለመሸከምና ከሕመም ነጻ ሊያደርገን አይደለም። ኢሳ. 53፥5 ስለ ነፍስ ደኅንነት

<u>እንጂ ስለ ሥጋ ጤንነት አይደለም የሚናገረው</u>። ይህን ካልን የጌታን ስቃይ ዓላማ ከትልቁ ወደ ትንሹ አውርደን ዓላማውን ማሳትና ማቅለላችንም ይሆናል።

ጌታ በብሉይ ኪዳንም በቀጥታም በሰው አማካይነትም ፈውሷል። ከሕመምና ከበሽታ ለመፈወስ በሥጋ መምጣት የለበትም። በመስቀል ላይ ሳይውልም፥ ገና ሳይገረፍም ብዙዎችን ፈውሷል። በማቴ. 8፥16-17 የተጻፈውን አሳብ ስንወስድ ይህ ጥቅስ የተጠቀሰው ገና ጌታ ሳይገረፍ፥ መከራ ሳይቀበል፥ ሳይሰቀልና ሳይሞት ነው። አዳኙና ፈዋሹ የተነገረለትም መሢሕ እርሱ መሆኑን ለማሳየት ይህ ጥቅስ ተጠቀሰ እንጂ የሰዎቹን ደዌ ለመሸከም ጌታ ገና በመስቀል ላይ አልዋለም ነበር። በመስቀል ላይ ከመዋሉ በፊት ድውዮችን ፈውሶ ነበር። ጌታ ሰዎችን ከደዌ ለማዳን የግድ በመስቀል ላይመዋል አልነበረበትም ሳይውልም ፈውሶ ነበርና። ለነፍሳችን ደኅንነት ግን መሰቀል ነበረበት፤ጌታ ባይሰቀል ኃጢአታችን አይወገድም፤ በኃጢአታችን ደግሞ እንሞታለን እንጂ አንድንም። የመስቀሉ ዓላማ እንግዲህ በግልጽ የነፍሳችን ደኅንነት እንጂ የሥጋችን ፈውስ አይደለም። የሥጋችን ፈውስ ጸጋውና ምርቃቱ እንጂ መብት አድርገን የምንወስደው ጉዳይም አይደለም።

የጴጥሮስንም አጠቃቀስ ስናይ ተመሳሳይ እውነትን ነው የሚናገረው። መናገርም ይገባዋል። የጥቅሶቹን ዙሪያ ስንመረምር ስለ ሥጋችን ሳይሆን ስለ ነፍሳችን ሲናገር ነው የምናየው። ጌታ የተሸከመው የሥጋችንን ሕመም ሳይሆን የነፍሳችን በሽታ የሆነውን ኃጢአታችንን ነው። በቁጥር 22-23 የመሢሕን ማንነት ይናገራል። በቁጥር 24 ጌታ ያደረገውን ነገር ከነዓላማው ይናገራል። ጌታ ያደረገው <u>በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ መሸከም</u> ነው። ሌላ ነገር ሳይሆን ኃጢአታችንን ነው የተሸከመው። ያደረገበት ምክንያትም <u>ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር</u> ነው። ለሌላ ከዚህ ላነሰ ነገር አይደለም።

የጌታን የመስቀል ሞት እኛን ከማዳኑ ባነሰ ነገር መለወጥ ትልቅና አደገኛ ስሕተት ነው። 'በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ' ሲል ሥጋዊ ፈውስን ያለመሆኑ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው። በቁጥር 25 ደግሞ ምን እንደነበርንና ምን እንደሆንን ይናገራል። በተለይ ወዴት እንደተመለስን ይናገራል። በርግጥ ጌታ የሥጋችንም ጠባቂና እረኛም ቢሆንም፥ ጴጥሮስ ግን 'ወደ ነፍሳችሁ ጠባቂ እረኛ ተመልሳችኋል' ነው የሚለን። ወደ ነፍሳችን ጠባቂና እረኛ። ጴጥሮስም የኢሳይያስን መጽሐፍ በመጥቀስ የሚነግረን ኢሳ. 53 ደኅንነት ሲል ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ደኅንነት መሆኑን ነው።

ታዲያ ይህ ማለት ጌታ ሥጋን አይፈውስም ማለት ነው? አይደለም፤ ይፈውሳል እንጂ። ጌታ ይፈውሳል? ቃሉስ ይህን ይናገራል? ጌታ በእርግጥ ፈውሷል። ወንጌላት ይህን ይመሰክሩልናል። ሐዋርያትም ፈውሰዋል፤ የሐዋርት ሥራ ይህን ይነግረናል። ወንጌል

ሲሰበክ ከሚከሰቱት ምልክቶች መካከል አንዱ የድውያን ፈውስ ነው፤ ማር. 16፥15-20። መፈወስ ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ ነው፤ 1ቆሮ.12፥9። በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞች ሲታመሙ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን እንዲጠሩና እንዲጸለይላቸው፥ እንደሚፈወሱም ተጽፏል፤ ያዕ. 5፥14-15። እነዚህ ሁሉ የጌታ ቃል የሚናገራቸው የፈውስ ኀልውና እውነታዎች ናቸው። ይሁን እንጂ የሥጋ ፈውስ የወንጌሉ ትንሽ ቁራጭ እንጂ ወንጌሉ በሙሉ ማለት አይደለም። ክርስትናም የዚህ ወንጌል መንገድ ከሆነ ወንጌሉ የሚነገርበት ቦታም ይህ የድነት አዋጅ የሚታወጅበት ቦታ እንጂ የሥጋ ፈውስና በረከት ብቻ የሚታጨድበት ቦታ መሆን የለበትም።

በዘመናችን ወንጌል በሥጋ የሚታይ ምልክት ካልታከለበት ወንጌል የመሆኑ እውነት አጠራጣሪ እየሆነ መጥቷል። እግዚአብሔር የወደደውን የሚያደርግ ሉዓላዊ አምላክ እንጂ የወደድነውን ብቻ የሚያደርግ አገልጋይ ባለመሆኑ ፈቃዱን ሊፈጽም ቦታው አይነካበት። እርሱ እግዚአብሔር ነውና የወደደውን ቢያደርግ ያድርግ ባያደርግ ደግሞ እንዲያደርግ ማን ያስገድደዋል? እግዚአብሔርቢፈልግ ሊሰጥ ወይም ሊነሣ፥ ሊጥል ወይም ሊያነሣ፥ የወደደውን ሊሾም ወይም ሊሽር፥ ሊገድል ወይም ሊያድን ይችላል። የፈቀደውን ካላደረገ እግዚአብሔርነቱ ወዴት አለ? እግዚአብሔር እኛ የወደድነውን ያላማድረጉ (ለምሳሌ፥ ያለመፈወሱ) ጨካኝ አያደርገውም። ደግሞ ቢሆንስ? ቢጨክንስ ማን ይቆጣዋል? ማን ይከለክለዋል? ያለመፈወስን ከመጨከን ጋር የሚያያይዘው የኛ ጠባብ አስተሳሰብ እንጂ እርሱ ምንን ለምን እንደሚያደርግ ማና መርምሮ ይደርስበታል?

ከላይ እንዳየነው ከእርግማን በታች በወደቀች ዓለም ነው የምንኖረው። ቅዱስ ቃሉ እንደሚያስተምረን አማኞችም እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ድረስ ከአካላዊ ስቃይ ሙሉ በሙሉ ነጻ አይወጡም። የክርስቶስ ምጽአት ጌታ ምድራዊ አካላችንን ሙሉ በሙሉ የሚዋጅበት ጊዜም ነው። (ሮሜ. 8፥19-25) አካላችንም ሙሉ በሙሉ የሚዋጀው የትንሣኤ አካል ስንለብስ ነው። ይህ የውጪው ሰውነት የሚጠፋና የሚበሰብስ ያኛው ደግሞ የማይጠፋ ነው። (2ቆሮ. 5) የአማኞችን ሥጋዊ ስቃይ ለመመልከት ከብሉይ ኪዳን ኢዮብን ከአዲስ ኪዳን ደግሞ ጳውሎስን እንይ።

የዚህ የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች በኢዮብ የደረሰበትን መከራና ስቃይ እራሱ በፍርሃቱና ‘አፍራሽ ንግግሩ’ በላዩ ያመጣቸው ነገሮች ናቸው ይላሉ። ለዚህም የሚጠቀሰው ኢዮ.3፥25 ነው። ነገር ግን በኢዮብ ላይ የሆነው እንዲሆን የፈቀደው ሌላ ማንም ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነው። ምንም እንኳ የሆኑት ነገሮች እንዲሆኑ ያደረገው ሰይጣን ቢሆንም ነገሮቹ እንዲሆኑም ሆነ ሰይጣን እንዲያደርግ የፈቀደው ልዑል እግዚአብሔር ነው። ይህን እውነት እንኳ እኛ የተገለጠውን መጋረጃ የምናይ

አንባቢዎች እንቅርና ኢዮብ ራሱ እንኳ መረዳት የሚችለውን ያህል ተረድቶ ነበር። ስለዚህም ኢዮብ እጅግ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ይዘን እንጂ ከታማኝነቱ ጥቂትም ፈቀቅ አላለም።

ሐዋርው ቅዱስ ጳውሎስስ?በ2ቆሮ.12፥7-9 ጳውሎስ ስለ *ሥጋው መውጊያ* ይናገራል። ይህ *የሥጋ መውጊያ* አንድ ወይም ሌላ ዓይነት ሕመም መሆኑን እንረዳለን እንጂ ምን ዓይነት በሽታ መሆኑን አናውቅም። ክርስቲያን መታመም የለበትም እንደሚሉ አስተማሪዎች ሕመም የሚመጣው ከኃጢአት ከአፍራሽ ንግግርና ካለማመን ከሆነ የጳውሎስ ችግር የትኛው ይሆን?በእጁስ ብዙዎችሐዋርያዊ ተዓምራት ተደርገው (ፈውስም ጭምር) እርሱ ግን ለምን ታማሚ ሆነ?ለምንስ የእግረ መንገድ አገልግሎትም ቢሆን ሐኪሙ ሉቃስ አብሮት እየዞረ እስኪያገለግል ድረስ አስፈለገ? ይህ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያውቅ ድንቅ አገልጋይ ለሕመሙ መወገድ ለምን ከአንዴም ሦስቴ መጸለይ አስፈለገው  ጽልዮ ለምን አልተፈወሰም? ስለ ጢሞቲዎስ የሆድ ሕመም በቃል ፈንታ የወይን መድኃኒት ማዘዙ ባለማወቁ ነው? (1ኛ ጢሞ.5፥23) ጥሮፊሞስንስ ታሞ በሚሊጥን የተወው ያልተረዳው ነገር በመኖሩ ነው?  (2 ጢሞ. 4፥20)አፍሮዲጡስ ስለ ምን ታሞ ለሞት ቀረበ? (ፊል. 2፥27) በጊዜው የፈውስ ስጦታ ስላልነበረ ነው ወይስ ለዘመናችን የእምነት አስተማሪዎች የተገለጠላቸው ጳውሎስ ያላወቀው ነገር ኖሮ ነው።

ኃጢያን ያልታመሙት ኃጢያን ስላለሆኑ አይደለም። ናቸውና ጻድቃንም ቢታመሙ ጻድቃን ስላልሆኑ አይደለም። ናቸው። ጽድቃችን በእኛ ሁኔታ ወይም በራሳችን የሚደረግ አይደለም። ክርስቲያኖች ችግር ወይም ሕምም ቢገጥማቸው እንደ ኢዮብ ወዳጆች በፍርድ በትር አንደብድባቸው በወቀሳና በማንኳሰስ ድንጋይ አንውገራቸው። ከእነርሱ የተሻለ እምነት አለ የምንል ከሆነ እምነታችንን ወደ ሜዳ እናውጣው ጸልየንላቸው ይፈወሱ ወይም ተግባራዊ በሆነ መንገድ እንደግፋቸው እንጂ እምነታቸውን አንናቀው። አንፍረድባቸውም።

መድኃኒትን ያለመውሰድ ሌላው የ 'ፈውስ' አስተማሪዎች የሚበረታቱት የሚያበረታቱት ትምህርት ነው። መድኃኒትን መውሰድን ልክ በሽታውን አሜን ብሎየመቀበልና ከበሽታውም ጋር የመተባበር ምልክት አድርገው ይወስዱታል። ከዚህም ትምህርት የተነሣ በጣም ቀላል በሆነ ህክምና ሊድኑ እየቻሉ የተሰቃዩ ኮማ ውስጥ የገቡና የሞቱ ሰዎች አያሌ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ መድኃኒት መውሰድን ይከለክላል? መደኃኒት መውሰድ ደካማነት ፥ ኅዶሎነት፥ ያለማመን ነው ይላል? መድኃኒት መጠቀምና በሐኪም መታየት ኃጢአት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ እንኳን ይህን ማድረግ ኃጢአት መሆኑን አይነግረንም። ማቴ. 9፥12፤ማር.2፥17 እና ሉቃ. 5፥31 ባለጤና ያልሆኑ ባለመድኃኒት እንደሚያስፈልጋቸው

ይነግረናል። ይህ ጌታ ራሱ የተናገረው ነገር ነው። እየተናገረ ያለው ምሳሌ ቢሆንም በምሳሌው ውስጥ እውነትን ነው እየተናገረ ያለው። ስለዚህ ሐኪሞች ሠራተኞች እንጂ የሰይጣን መሳሪያዎች እንዳልሆኑ ከቃሉም እንረዳለን። ሐኪሞችም ቢፈውሱን እነርሱን ተጠቅሞ የፈወሰን እግዚአብሔር መሆኑን በማሳሰብ ጆን አር. ራይስ የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑር ሲጽፍ፤

> በመጀመሪያ መታመናችን በሰው ሳይሆን ሁሌም በእግዚአብሔር መሆን እንዳለበት እናስታውስ። እግዚአብሔር ሐኪሞችን ሊጠቀም ይችላል ተጠቀሞም በሽታን ሊያድን ይችላል። ብዙ ጊዜ ያለ ሐኪም፥ያለ መድኃኒትም በጸሎት ብቻም ይፈውሳል። የሆነ ሆኖ በየትኛውም ቢሆን በሐኪምና ያለ ሐኪም ወይም በመድኃኒትና ያለ መድኃኒት በእግዚአብሔር መደገፍና እርሱ ለሥጋችን ጥንቃቄና ለሕመማችን ፈውስ የሚያዘጋጅልንን መፍትሔ ልንቀበል ይገባናል።... ማስጠንቀቂያ በአጭሩ ይህ ይሁን ሁሌ ችግራችንን ወደ ጌታ ዘንድ ማቅረብ አለብን። አንዳንድ ጊዜ ምሬቱ ሐኪም ወይም መድኃኒት ወይም ኦፐሬሽን መሆን እንዳለበት ግልጽ ይሆንልናል አንዳንዴም ሌላ መፍትሔ ይኖረዋል፤ ነገር ግን ሁሌም መታመናችን በእርሱ ዋናው አሳባችንም የእርሱን ፈቃድ አውቀን እርሱን ማስደሰት ይሁን። [34]

ኢሳ.1፥6 እና ሉቃ. 10፥34 በቁስሎች ላይ ስለሚቀባ ስለሚያለዝብ ዘይት ይናገራል። ኢሳ.38፥21 ነቢዮ ኢሳይያስ የበለስ ጥፍጥፍ አምጥተው በንጉሡ በሕዝቅያስ እባጭ ላይ እንዲለጥፉና እንደሚፈወስም ተናገረ። በኤር.8፥22 ''በገለዓድ የሚቀባ መድኃኒት የለምን? ወይስ በዚያ ሐኪም የለምን? የወገኔ ሴት ልጅ ፈውስ ስለምን አልሆነም?''ይላል። የተናገረው ስለ መንፈሳዊ ፈውስ ቢሆንም ገለዓድ በዚያ ዘመን ብዙ መድኃኒቶች የሚሰሩባትና የሚቀመሙባትም ስፍራ ነበረች። (ኤር. 46፥ 11)ከማር.15፥23 እንደምናብበው ደግሞ ከርቤ የተቀላቀለበት የወይን ጠጅ እንደማደንዘዣ በመሆን ስቃይን እንደሚቀንስ ይታያል። በ1ጢሞ.5፥23 ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ለሆዱ ህምም ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲወስድ ነገረው። በማቴ 9፥12 እና ሉቃ.4፥23 ጌታ ስለ መድኃኒት መጥቀሱ በጊዜው ይህ የሐኪሞች ተግባርና የህክምና ሙያ የተለመደ መሆኑን ይነግረናል። የጳሎስ የቅርብ አባሪ አገልጋይ የነበረው ሉቃስ ሐኪም ነበር። ቆላ.4፥14'ባለመድኃኒት' ይለዋል። ከምሳ. 17፥22 እምደምንገነዘበው ደግሞ ስነ ልቦናዊ መድኃኒት መኖሩንም አይሁድ ሳያስተውሉ አልቀሩም። ከዚህም ባሻገር አይሁድ እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑንም ያውቁ ነበር። እግዚአብሔር ፈዋሽ እግዚአብሔር ነው። (ዘጸ. 15፥26) ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ማመን ህክምናን ያለመቀበል ማለት አይደለም። ወይም መታከም ማለት እግዚአብሔርን መካድ ማለት አይደለም። እግዚአብሔርን ትቶ ባለ መድኃኒቶችን ብቻ በመፈለግ አሳ ተሳስቶ ነበር። (2ዜና. 16፥12) የአሳ ስሕተት ባለመድኃኒቶችን መፈለጉ ሳይሆን እግዚአብሔርን ያለመፈለጉ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች እንደምናነበው እግዚአብሔር ያለ መድኃኒት እንደሚፈውስ ሁሉ በመድኃኒትም ይፈውሳል። ስለዚህ

መድኃኒትን መውሰድ ማለት መፈወስ የማይችለውን እግዚአብሔርን መርዳት ማለት አይደለም። ወይም ኃጢአት አይደለም።

አንዳንድ የፈውስ ጉባኤዎች በሚደረጉበት ጊዜና ከመደረጋቸው በፊት የፕሮግራሙ ዜና በስፋትና በጥንካሬ ይሰራጫል። ብዙዎችም ህሙማን እንዲጸለይላቸው አገር አቋርጠው ሳይቀር ይመጣሉ። እግዚአብሔር የሚፈውስም አምላክ ነውና የሚፈወሱ ይኖራሉ። ይህ ግሩም ነገር ነው። ይሁን እንጂ የአንዳንዶቹ ህመምተኞች ፈውስ ስሜታዊና እዚያው በስብሰባው ቦታና ሞቅታ ያውም ለቅጽበት ብቻ የሚሆን ሲሆን ትንሽ ቆይተው መማቀቅ ይጀምራሉ። የአንዳንዶቹ ደግሞ ምንም እንኳ የሚጸለዩላቸው ሰዎችም ሆኑ እነርሱም እራሳቸው መፈወሳቸውን ደጋግመው ቢናገሩም ፈውሱ ያልመጣላቸው ሆነው ተገኝተዋል። እንዲህ ካሉት ሰዎች ከፊሉ የእምነታቸውን ጎዶሎነት ሲያማርሩ ከፊሉ ደግሞ በአምላካቸው አማርረው እምነታቸውንም ይጥሉታል። በየትኛውም መንገድ ግን '' ድናችኋል... ፈውሳችሁን ተቀበሉ'' ያሉአቸው ሰዎች ከተጠያቂነት ነጻ ይሆናሉ። ላለመፈወስ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱት የፈውስ ስጦታ አለን የሚሉት ሰዎች ሳይሆኑ የበሽተኞቹ ጎዶሎ እምነት መሆኑን በብዙ ማስረጃ ሊረጋገጥ ይሞከራል። በአዲስ ኪዳን እንደምንመለከተው ግን እግዚአብሔር ከፈቃዱ የተነሣ ያልፈወሳቸው ሰዎች ቢኖሩም ፈውስንና እምነትን ካጣበቅናቸው ዘንድ ያለ መፈወስን የምናነብበው ከበሽተኛው ሳይሆን ከሚጸልዩት ሆኖ እናገኘዋለን። (ማቴ.17፥14-21) በዚህ ክፍል እንደምናየው ይህ ሰው ያልተፈወሰው ከራሱ ሳይሆን ከጸላዮቹ እምነት ጎደጎነት የተነሣ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው ሰው በጅማ ስብሰባዎች ላይ ስለሚገለጡ ፈውሶች አወዛጋቢነት ሲጽፍ እንዲህ ብሎአል።

> በፈውስ ስብሰባዎች ስለሚሰጡ አስቀድሞ የታቀዱ ሥነ ልቦናዊ ነገሮች ማለትም ሰዎች ሊፈውሱ እንደሚችሉ እንደሚፈውሱ እና እንደተፈወሱም እንዲያምኑ ስለሚደረገው ነገር ብዙ መዘርዘር ይቻላል። አስታውሱ ፈውሶች የሚደረጉት ሁሌም መዝሙር ባለበት ብዙ ስሜታዊ ነገሮች በሚገለጡበት የእግዚአብሔር ኃይል የግድ በሚባልበት የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሌም ፈውስ መሆኑ በሚነገርበት ወዘተ የጉባኤ አገልግሎት ነው። ብዙዎቹ የሰለላቸው ፈዋሾች ትልልቅ እዩን ባዮች ናቸው። እየታየ ያለው በያዕ. 5፥14-16 እንደተሳለው ያለ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ ቤታቸው ወይም ወደ ሆስፒታል አልጋቸው ጠርተው ለበሽተኞች እንዲጸልዩ የተባለው ጸጥተኛ አገልግሎት አይደለም። እየተፈለገ ያለው ይህ ሳይሆን በስሜታዊ ደስታ መሞቅ የትልቅ ጉባኤ ሥነ ልቦና እና የናፍቆትና የምኞት መገንባት ነው።[35]

ለበሽተኞች መጸለይ ጌታ ያዘዘውም ያስተማረውም ብቻ ሳይሆን መፈወስ እርሱ ምሳሌያችን በመሆን ያደረገው ነው። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑ የማይካድ እውነት የመሆኑን ያህል በአንጻሩ ደግሞ በጌታና በፈውስ ስም የሚደረጉ መስመር

የሳቱ ነገሮችም መኖራቸው ገሃድ ነው። ከቅርቦቻችን እንኳ ጥቂት ሰዎችን ብንጠይቅ ተጸልዮላቸው የተፈወሱ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ድናችኋል ተብለው በእርግጠኝነት የተነገራቸውና ያልተፈወሱ ሰዎችም አሉ። እንዲያውም ፈውስ ከታወጀላቸው በኋላ ከጥቂት ሰዓታት እስከ ጥቂት ቀናትና ሳምንታት ቆይተው የሞቱ ጥቂት ያይደሉ አሉ። የዚህ ዓይነቱ ነገር በጌታም ሆነ በሐዋርያቱ ተደርጎ ከሆነ የት ነው የተጻፈው?

(ማር. 8፥22-26 ዕውሩን ሰው ጌታ ከፈወሰው በኋላ ጠየቀው። መጀመሪያ ጌታ እጁን በጫነበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ አጣርቶ አላየም ነበር። ጌታ ሲጠይቀውም እውነቱን ከመናገር አለተቆጠበም ነበር። ሰዎችን እንደ ዛፍ ማየቱን ባይናገር ሰዎችን ከዛፎች ለይቶ የማየት ጤነንት ባልተሰጠውም ነበር። ጌታ ይህን ሰው ባንዴ መፈወስ ተስኖት አልነበረም ደረጃ በደረጃ የፈወሰው ምናልባት ለደቀ መዛሙርቱ ሊያስተምራቸው የወደደው ነገር ኖሮት ይሆናል። ዛሬ አንዳንዶች (በቁጥር ጥቂት ያልሆኑ ማለትም ይቻላል) የፈውስ ስጦታ አለን የሚሉ ወይም አላቸው የሚባሉ ሰዎች ለሕሙማን ከጸለዩ በኋላ በሽታው መጥፋትና ያለመጥፋቱን ለማረጋገጥ ስለ ሕመማቸው መጠየቅን አይወዱም ብቻ በደፈናው እንደ ተፈወሱ መናገርና በሽታው እንደሌለ መቁጠር እና ማስቆጠር ይቀልላቸዋል። ነገር ግን ጌታ እንዳደረገ ፈውስን ለማረጋገጥ አንድ ወይም ሌላ ነገር ማድረግ ድንቅ ነገር ነው። የጌታ ፈውስ የተረጋገጠ ፈውስ ነው። እዚያውና ወዲያው ወይም እየሄዱ እንደተፈወሱት ለምጻሞች ብዙ ሳይቆይ የሚደረግ ነው። በማቴ 8፥16 ጌታ ያደረገውንና በሐዋ. 5፥16 ሐዋርያት ያደረጉትን ስናስተውል ሁሉ እንደተፈወሱ እናያለን።

በአንዳንድ የፈውስ ስብሰባዎች የሚፈወሱ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። ከተፈወሱትም የአንዳንዶቹ ፈውስ አካላዊ ሳይሆን ስነ-ልቦናዊ ብቻ ነው። የተፈወሱ እንዲመስላቸው ይደረጉና እውነትም ይመስላቸዋል። ነገር ግን ስነ-ልቦናዊ ፈውስ አካላዊ ፈውስ መምሰል እንጂ መሆን አይችልም። በእንዲህ ያሉ ስብሰባዎች ሞቅታና ግለት ወቅት በስሜት መወሰድና ያልሆነው የሆነ የሚመስልበት ሁኔታ ይኖራል። ጌታም ሆነ ሐዋርያቱ በመላ-ምት አልነበረም ፈውስን ያደረጉት። የዘመናችን አንዳንድ አገልጋዮች ግን በነሲብ ነው በሽታውንም ፈውሱንም የሚናገሩት። በሽተኛው የተቀመጠበትን ቦታም ሆነ የበሽታውን ዓይነት በመሰለኝ መናገር የተለመደ ነው። 'በስተግራ በኩል እመጨረሻ አካባቢ የተቀመጥክ ወይም የተቀመጥሽ... ግራ ወይም ቀኝ ጆሮህ ገደማ... በስተ ጎንህ በኩል የሚያምህ ወይም የሚያምሽ... ' ወዘተ ይባላል። ይህ መላ-ምት እንጂ መገለጥ አይደለም። ለነገሩ ''መገለጥ'' የሚባል የጸጋ ስጦታም የለም። አንዳንዶቹ አገልጋዮች ደግሞ የጉባኤ ፈውስ አገልግሎት ሲያካሂዱ የሚታዩና የሚታወቁ በሽታዎችን ስም አይጠሩም መኖራቸውም ሆነ ፈውሱም የማያስታውቀውን በሽታ

ብቻ ነው ደጋግመው የሚጠሩት። አንዳንዶቹ ደግሞ ከአንድ ዓይነት በሽታ በቀር የሚያውቁም አይመስሉም። ልክ በጥቂት በሽታዎችላይ ልዩ ስልጠና የወሰዱ ዶክተሮች ይመስል ሁሌ ቢጠሩ እርሱን ነው። ሌሎች ደግሞ የሚፈውሰው እግዚአብሔር ሳይሆን ሲጸልይ የሚባለው ነገር እየመሰላቸው የፈውስ ቀመር በመኮረጅ ሰዎችን በተለይም አማኞችን ያወናብዳሉ። በተለይ በመኮረጅ የሚመጣው ጣጣ ብዙ ነው።

አንዳንድ የፈውስ አገልጋዮች በዚህ አገልግሎት ረገድ ከረር ያለ አቋምና ራቅና ጠምዘዝ ያለ አዝማሚያ ይወስዳሉ። በዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ እንደ ጀማሪና መሪ የሚታየው ቻርልስ ፎክስ ፓርሃም ሰማያዊ ፈውስ የሁሉም አማኝ መብት እንደሆነ አስተምሮ ነበር። አንዳንድ አስተማሪዎች የመንፈሳዊ ሰዎች መታመም ግራ ሲገባቸው ሌሎችም በሰይጣን ያመካኛሉ። ሌሎች በሽታን እንደ ኃጢአት በሽተኞችን አንደ ኃጢአተኞች ይቆጥራሉ።

ሆባርት ፍሪማን የተባለ መጀመሪያ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረና በ1960ዎቹ ካሪዝማዊ ንቅናቄ የተወሰደ ሰው ነው። ይህ ሰው በአሜሪካ አገር በኢንዲያና ግዛት የእምነት ጉባኤ የተባለውን ቤተ ክርስቲያን ጀመረ። በርሱ እምነትና ትምህርት መሠረት ሕክምና ከጥንታዊ ጥንቆላ የመነጨ በመሆኑ መድኃኒት መውሰድና ሐኪም ቤት መሄድ ለሰይጣን አሰራራር መጋለጥ ነው። ስለዚህ የርሱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሐኪም የላቸውም ሴቶች ሲወልዱ እንኳ ሆስፒታል አይሄዱም። በቤት ውስጥ መውለድ በአገራችን የተለመደ ቢሆንም ይህ ግን አሜሪካ ነው! ከዚህ የተነሣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መመስረት እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ድረስ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊታከሙና ሊድኑ የሚችሉ ከመቶ የማያንሱ ሰዎች ሞተዋል። በአንዲት የ15 ዓመት ልጃገረድ ሞት ምክንያት ወላጆችዋ በግድየለሽነታቸው ተከሰሰው የ10 ዓመት እስራት ተፈርዶባቸው ነበር። ራሱ ሆባርት ፖሊዮ ከሚባል የእግር በሽታ ተፈወስኩ ቢልም በዲሴምበር 1984 ሲሞት በሳምባ ምችና እየባሰበት ከሄደው ከእግሩ ሕመም ጋር በተያያዘ የልብ መድከም ተጠቅቶ ነበር። ሆባርት የተጎዳው ከሕመም ይልቅ በራሱ ትምህርት ነበር ማለት ይቻላል።

ዛሬም ይህን የሚያስተምሩ አስተማሪዎች በብዙ የሚቆጠሩ ናቸው። በርግጥ ከሆባርት በፊት ሌሎችም ፈውስ የክርስቲን መብት መሆኑን ያስተማሩና የፈውስ ስጦታ እንዳላቸው የተናገሩ የነበራቸውም ግን በሕመም ይሰቃዩ የነበሩ ሰዎች አሉ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በጣም ዝነኛ የሆነው የፈውስ አገልጋይ ዊሊያም ብራንሃም በ1965 የመኪና አደጋ ደርሶበት ስድስት ቀናት ታሞ ሲሞት ተከታዮቹ ብራንሃም እንዲፈወስ ጸልየው አልሆን ማለቱ ሳይታክታቸው ከሞተ በኋላ ከሞት እንዲነሣም ጸልየውለት ነበር። ሌላው አገልጋይ ኤ.ኤ.አለን በ1967 በጉበት በሽታ ነበር የሞተው፥ ይጠጣ ነበርና። ካትሪን ኩልማን ወደ 24 ዓመታት ያህል ስታገለግል ቆይታ

በ1976 ሞተች። በምታገለግልባቸው ጊዜያት የልብ ድካም ነበረባት። ሩት ካርተር እስቴፕልተን (የጂም ካርተር እህት) የፈውስ አገልጋይ ሆና ስታገለግል ኖራ ከንሰር እንዳለባት ስታውቅ ለመታከም ፈቃደኛ አልነበረችም፤ በ1983 ሞተች፤፡ በዚህም ዘመን በመሰል አገልግሎት የተሰማራው ጆን ዊምበር የልብ ታማሚ ሲሆን መታመሙን አልካደም መድኃኒትም ይወስዳል። በቴክሳስ እምነት ፈውስ አገልጋይ የነበረው ጃክ ኮው‘ፈውስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፥ ያለመፈወስም ከእምነት ጎዶሎነት ብቻ የሚመጣ ነው’ በማለት ሲያስተምር ቆይቶ ራሱ በፖሊዮ በሽታ ታሞና በሆስፒታል ውስጥ ቆይቶ በ38 ዓመቱ ነበር የሞተው።

ይህን ክፍል ስናጠቃልል የበሽታንም ምንጭ በትንሹ እንይ፤፤ በሽታ ሁሌም ከሰይጣን አይደለም የሚመጣው። ወይም ካለማመን አይደለም የሚወለደው። ከተለያዩ ምንጮች ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ሊመጣብን ይችላል። የበሽታን ምንጭ ማወቁ ለመጠንቀቅም ሆነ ለመከላከል ይረዳናል። ጥቂቶቹ ከታች የምናያቸው ናቸው።

<u>የተፈጥሮ ሕግን መጣስ</u>። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው ከስድስተኛ ፎቅ በረንዳ ላይ ልክ መሬት ላይ እንዳለ አድርጎ ቢራመድ ወድቆ ይሰበራል ወይም ይሞታል። የተፈጥሮን ሕግ ማለትም የመሬት ስበትን ሕግ ስለጣሰ። ወይም አንድ ሰው ከመጠን በላይ እየሰራ በቂ እንቅልፍ ባያገኝ ይታመማል። አካል በተፈጥሮው እንዲያርፍም ተደርጎ ነው የተሰራው፤፡

የኃጢአት ውጤት። እግዚአብሔር አታድርጉ የሚላቸውን ነገሮች በመተላለፍ ሰዎች በአካላዊ፥ አዕምሯዊና መሰል በሽታ ሊጠመዱ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ''አታመንዝር'' የሚለውን ትዕዛዝ የተላለፈ አንድ ሰው ዝሙት ወለድ የሆነ ደዌ ዒላማ መሆኑ አይቀሬ ነው።

በንዝህላልነት። ለምሳሌ፥ ጤንነትን በሚጎዱ ንጽህና በጎደላቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያለ ምንም ጥንቃቄ መቆየት ወይም በቂ ልብስ ባለመልበስ ለብርድ መጋለጥ።

በውርስ ከወላጆቻችን የሚመጣብን። አንዳንድ ሕመሞች ከወላጅ ወደ ልጅ የሚተላለፉ መሆናቸው ግልጽ ነው።

ሰይጣን ሊያመጣብን ይችላል። (ሉቃ.13፥10-17 በተለይ ቁ16) ጌታን የሚያውቁትን ሁሉ ሰይጣን የሚጎዳበት ስልጣን የለውም። ከኢዮብ መጽሐፍ እንደምንመለከተው ግን ተፈቀደለትን ያህል ብቻ ሊያደርግ ይችላል።

የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ። በዮሐ.9፥3 እንደምናገኘው ያ ሰው ዕውር ሆኖ የተወለደው ደቀ መዛሙርቱ እንደገመቱት እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት ስለሰሩ ሳይሆን የጌታ ክብር እንዲገለጥ ነው። ሰውየውም ሆነ ወላጆቹ ኃጢአት የሌለባቸው ንጹኃን ናቸው ማለት አይደለም ግን ሕመሙ የዚያ ውጤት አልነበረም። የዕውሩ ዓይኖች ስለበሩ የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ መታየቱ ግልጽ ነው። የአንዳንድ ሕመም ውጤቱ ቢመስለንም ባይመስለንም የጌታ ክብር ነው። 'እኔ እተሰቃየሁ ጌታ እንዴት ይከብራል?' ልንል እንችል ይሆናል፤ ቁም ነገሩ መከበሩን ማወቃችን እንጂ እንዴት እንደሚከብር መረዳታችን አይደለም። ለኛ በማይገቡን ነገሮች ጌታ እንዴት እንደሚከብርና በየትኛው ይበልጥ እንደሚከብር መጨነቅ የራሱ ስራ ነው መሆን ያለበት።

ቻርልስ ሃሜል የተባለው ጸሐፊ ስለፈውስ አገልግሎት ሲጽፍ ኢሳ.53፥5ን ጠቅሶ የሚከተለውን አሳብ ይሰነዝራል።

> *በዚህ (ጥቀስ) መሠረት እምነታቸውን በመለማመድ ቅጽበታዊ ፈውስን እንዲያገኙና ከዚያ በኋላ የሕመም ምልክቶች መኖራቸው ቢቀጥልም እንኳ በዚያው እንዲቀጥሉ ይስተማራሉ። ስለ ሕመሙ ምልክቶች መቀጠል መጨነቅ እንደ ኀዶሎ እምነት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። እንዲያውም በስቃይ ውስጥ ያለ ሰው ፈውስን ከማግኘት ይልቅ ያገኘውን ለመጠበቅ ይበልጥ እምነት እንደሚያስፈልገው ይነገረዋል።*
>
> *በዚህ ረገድ የሚመጣው ጉዳት በብዙ መንገድ የሚገለጥ ነው። ካልጠፋው የሕመም ምልክት ችግር ጋር መታገሉ የወንጀለኝነትና የጭንቀት ሸክም ይፈጥራል። 'በእውነት ድኛለሁ? ከሆነስ የሕመም ምልክቶች ለምን ይኖራሉ? ሐኪም ማየት አለብኝ?'በሚል አሳብ ይወዛወዛል። በመካከሉ ደግሞ ሕመሙ ጥንቃቄ ሳይደረግለት በመቀጠሉ ምልክቶቹ ይብሳሉ። ተስፋ በመቁረጥ ሐኪም እስኪታይና ሐኪሙም ምንም ዕርዳታ ሊያደርግ እስከማይችል ይደረሳል። በሽተኛው በመጨረሻ የሕክምና መስመር ውስጥ ሲገባም እምነትን አንደካደና እግዚአብሔር የሰጠውን 'ፈውስ' እንቢ እንዳለ እንዲሰማው ይደረጋል። ባልጠፋው ሕምም ላይም የአጥፊነት ሸክም ይጨመርበታል። የጸጋ ስጦታ መሆን የነበረበትም ነገር በውሸት እምነት ተባለ የሃይማኖት ስራ ይሆናል። እንዲህ ያለው ሕመምተኛ በመጨረሻ ወደ እነርሱ ሲመጣ ሐኪሞች 'የእምነት ፈውስ' ስለሚባለው ነገር መጥፎ ቃላት ቢናገሩ አያስገርምም።*
>
> *የደኅንነት የመጨረሻ ዓላማ እኛን ሙሉ ማድረግ ቢሆንም የኢሳ.53፥5 ዓውድና አባባል የሚያመለክተው የኃጢአታችንን ስርየት ነው። በተጨማሪም ቅጽበታዊ ፈውስ የክርስቲን መብት መሆኑን ወይም ፈውስን ከመቀበል ይልቅ ማቆየቱ የበለጠ እምነት እንደሚጠይቅ አዲስ ኪዳን አያስተምርም። እግዚአብሔር በርግጥ በጤንነት በኩል ይቆማል ነገር ግን ብዙ ጊዜ የማንረዳቸው ችግሮች ሙሉነታችንንም ሆነ ቅድስናችንን ያደናቅፉታል። በተጨማሪም አንድ ሰው በተአምር ሲፈወስ ምልክቶቹ በሙሉ እንደሚጠፉና ሁሉም ደግሞ እንደሚያውቁት መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርገዋል። ሽባው ተነሣና ምንጣፉን ተሸክሞ ወጣ፥ ማንም ሊይዘው ያልቻለው የጌርጌሴኖኑ ዕብድ ፀጥ ብሎ ተቀመጠ ለበሰና ደህናም ሆነ። ፈውሳቸውን ለመጠበቅ እምነታቸውን የተለማመዱበትን ምንም ምልክት አናይም።*[36]

ለማጠቃለል ፈውስ በቃሉ ውስጥ ያለ እውነት በመሆኑ የፈውስ ስጦታ ባላቸው አገልጋዮችም ሆነ በያዕ 5 መሠረት በሽማግሌዎች ዘይት መቀባት አማካይነት ለሕሙማን መጸለዩ ተገቢ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ነው። ጸልዩ ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተውም መደረግ ያለበት ነገር ነው። በአንጻሩ ደግሞ ሰዎች ባይፈወሱ እንኳ ይህን ፈርቶ መጸለይን ያለመተው አስፈላጊ ነገር ነው። የሰዎችን እምነት በፍርድ ዱላ መደብደብ ግን በቃሉ ውስጥ ያየናቸው አገልጋዮች ያላደረጉት በዘመናችን እየታየ ያለ አዲስ ዓይነት 'አገልግሎት' ነው። ይህን አጉል ዱላ በፍርሃትና በለዘብታ ማለፍ የለብንም። ምክንያቱም ይህ የሰዎችን እምነት የሚያፈርስ የሰዎች ብቻ በትር እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም።

# የኤድስ 'ፈውስ'

# (ከመቅአስ መጽሐፍ)

[ይህ ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ እና የአፈታት ስሕተቶች መጽሐፌ የአፈታት ስሕተቶች ከሚለው ምዕራፍ፥ አስተውሎት ከሚለው ስር የተጻፈና ከዚያ የተወሰደ ነው። በሁለተኛው እትም ከገጽ 323 ጀምሮ ይገኛል።]

የአንዳንድ 'ትልልቅ' ሰዎች አገልግሎቶች በትልልቅ 'ተአምራት' የታጀቡ ናቸው። አሳዩን፥ አቅርቡልን ሲባል ግን እነሱም ምልክቶቻቸውም የሉም። ለምን? 20ና 30 ዓመት ያገለገሉ ጉምቱ አገልጋዮች እንዴት ተብለው ይጠየቃሉ? በተለይ 40 ዓመት ዳቦ ተቆርሶ ሻማ በርቶ ካከበሩ በኋላ ምን ተብሎ ይጠየቃል? ነውር አይደል?

ቤኒ ሂን በ'ፈውሶቹ' በጣም ስሙ የተጠራ ሰው ነው። ሃንክ ሃነግራፍ የተባለ መካቴ ክርስትና ቤኒ ሂንን፥ 'እውነተኛ ድውያን የነበሩና እውነተኛ ፈውስ በአንተ በኩል የተቀበሉ 3 ብቻ ሰዎች አመልክተኝ።' ብሎ ጠይቆት ነበር። ቤኒ ለሃንክ የሰጠው ሦስት ፈውሶች የውሸት መሆናቸውን ማረጋገጡን ሃንክ ተናግሮአል። እኔም ከአገራችንን ፈውሰኞች አንድ ሦስቱን ስለ ኤድስ ፈውሳቸው ማረጋገጫ ጠይቄ አለማግኘቴን በማኅበራዊ ሚድያዎች አጋርቼ ነበር። ይህንን ጥያቄ ማቅረቤን መጻፌ በራሱ እንደ ትልቅ የነውር ተግዳሮት ተቆጥሮ ነበር። የጠየቅኋቸው ሰዎች፥ በናሙና ስብከት ክፍል የጠቀስኩት ዶ/ር ዳን ስለሺ፥ መጋቢ ሰይፉ ከበደ፥ እና ወንጌላዊ ደሳለኝ አላቤ ናቸው። ይህንን ባካፈልኩ ጊዜ፥ ያልተፈወሱት ሰዎች ሳይፈወሱ፥ 'ተፈውሳችኋል!' መባላቸው ሳያስቆጣቸው ስም መጥቀሴ ነበር ብዙዎችን ያስቆጣቸው። ይልቁን ማስቆጣት የነበረበት የውሸቱ ፈውስ መሆን ነበረበት። በተገላቢጦሽ፥ 'አንተ ማን ሆነህ ነው አገሌን የምትናገር?' ተባለ።

እግዚአብሔር ፈዋሽ እና ተአምር አድራጊ አምላክ መሆኑን ሳንተው፥ ሰውን መጠርጠር እኮ እግዚአብሔርን መካድ አይደለም! የአንዳንዶቹ አገልጋዮቻችን 'ግዙፍነት' የሚያንገዳግደን ስለሆነ፥ የሚወድቁብን ስለሚመስለን የሚሉትን ምንም ሳንጠይቅ እንቀበላለን። እነሱን መካድን እግዚአብሔርን መካድ ያስመስሉታል። ፈውስ እኮ በሰውነታችን የምናውቀው ነገር ነው። ጌታን ዳስሳ ስለተፈወሰችው ሴት ማርቆስ ሲጽፍ፥ *ወዲያውም የደምዋ ምንጭ ደረቀ ከሥቃይዋም እንደዳነች በሰውነትዋ አወቀች።* ማር. 5፥29 ነው ያለው። በሰውነትዋ አወቀች። ዕውር ካየ እኮ እያየ ነውና አይጠየቅም፤ አይጠረጠርም። ሽባ አልጋውን ተሸክሞ ሲሄድ፥ 'እውነት ተፈውሰህ ነው የምትራመደው?' ብሎ ማን ነው አቁሞ የሚጠይቀው? ማን ይጠረጥራል? በርጤሜዎስን፥ 'እውነት ታያለህ? እውነት እየታየህ ነው የምትራመደው?' ማን ይላል? የሚያስጠይቀው ውሸታሙ ነገር ደግሞ ቢጠየቅ ምን ችግር አለው?

በካሪዝማውያንና ጴንጤቆስጣዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እጅግ በዝቶና ተጋንኖ የሚደረግ አንድ ቀውስ የፈውስ ቀውስ ነው። ከላይ እንዳልኩት በስብከትም በመጽሐፋቸውም ትልልቅ ፈውሶች በእጃቸው እንደተከናወኑ በድፍረት የሚናገሩ ጥቂት ሰዎችን እነዚያን የተፈወሱ ሰዎች ማንነት እንዲነግሩኝ ጠይቄ ከአንዳቸውም እንደዚያ ያሉ የተጋነኑ ፈውሶችን እንዳረጋግጥ ስምና አድራሻ የሰጠኝ የለም። የዚህ ዓይነቱ አካሄድ በአገራችን የተለመደ ነገር አይደለም። እንኳን ለማረጋገጥ መጠየቅ፥ መታሰቡ ራሱ ከኃጢአት ይቆጠራል። ሰዎቹን መጠርጠር ሳይሆን እግዚአብሔርን መካድ ተደርጎ ይታያል።

በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ ውስጥ፥ 'የፈውስ ቀውስ' በሚለው ንዑስ ርእስ ስር የተጠቀሰ በመቱ የተደረገ የፈውስ ጉባኤ ላይ ልትፈወስ ሄዳና 'ተፈወሰች' ተብላ እመድረክ ላይ ስለሞተችውና ሬሳዋ ስለወጣው ሴት ተወስቶአል። በዚያው ሴቲቱ የሞተችበት ጉባኤ ላይ የተነገረ ሌላ ፈውስም ነበረ። የኤድስ ፈውስ። በዚያ የነበረ አንድ ወጣት የኤድስ በሽታ እንዳለበትና እንደተፈወሰ ያው በዚያ የተጠቀሰ ፈውሰኛ ተናገረ። የከተማዋ ሕዝብ እስኪሰሙት ድረስ ይህ የፈውስ ዜና ተስተጋባ። እኅቱም፥ 'የሰው አፍ የገባው ወንድሜን ጌታ ኀበኘው!' እያለች ብዙ የምስጋና ምስክርነት ቃል ተናገረች። በማግስቱ በነበረው ቀጣይ የፈውስ ጉባኤ ላይ

የተፈወሰው ወጣት እንዲመሰክር ጊዜ ተይዞለት ነበር። ቢጠበቅ የለም፤ ሲፈለግም በአምቡላንስ ወደ ሆስፒታል መወሰዱ ተሰማ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሆስፒታል ወጣ። ግን፥ ድኖ ሳይሆን በዚያው ሕመም ሞቶ ሬሳው ነበር የወጣው።

ሌሎችም ጥቂት ያልሆኑ በኤድስ የተያዙና እንደተፈወሱ በግልም በአደባባይም እየተነገራቸው ግን የሞቱ ሰዎችን አውቃለሁ። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ሰዎችን ከምንም ዓይነት በሽታና መቅሰፍት ሊያድን እንሚችል ፈጽም መጠርጠር የለብንም። እግዚአብሔር ሊፈውስ ይቻለዋል፤ ግን የውሸት ፈውሶችን እንደ እውነት መቀበል በክርስቶስ ከማመናችን ጋር አብሮ የተሰጠን ግዴታ አይደለም። ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን እንደተፈወሱ ከመቀበል ብቻ ባሻገር ማረጋገጥ አስፈላጊና እንደ ዘበት ሊታለፍ የማይገባው እውነት ነው። ከኤድስ እንደተፈወሰች ከተነገራት አዘውትሬ ከምሄድባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለች አንዲት ልጅ የፈውስ ማረጋገጫ ለማግኘት ሞክሬ ነበር። ያገኘሁት መልስ ግን ይህንን ማረጋገጫ ለማግኘት አሳቡን ራሱን ማስተናገድ ተመልሶ በበሽታው ጭንቀት ራስን እንደማጠላለፍ ብቻ ሳይሆን እንደ አለማመንም እንደሚቆጠር ነበር። መጠየቁም እምነትን እንደ መናድ እንደሚያስቆጥርም ነው የተነገረኝ።

ተአምራት በሚል ርእስ በፓስተር ሰይፉ ከበደ የተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ ጸሐፊው ካያቸው ተአምራት ዝርዝር ውስጥ የኤድስ መመታትም ይገኝበታል። የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ባልጠራጠርም የሰማኋቸውና የገጠሙኝ የኤድስ ፈውሶች ሁሉ ውሸት ሆነው ስላገኘሁ ተጨባጭ መልስ ለማግኘትና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎችን ስምና አድራሻ ከደራሲው ጠይቄ ነበር። እስከዚህ ጽሑፍ ሕትመት ድረስ መልስ አላገኘሁም። እስከ ሁለተኛው እትምም ድረስ መልስ የለም።

ከላይ በናሙና ኮንፈረንስ ምዕራፍ የተጠቀሰው ሰባኪ አሁን ከምኖርበት ስፍራ ባልራቁ ሁለት የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ከኤድስ የተፈወሱ ሰዎች መኖራቸውን በዚያው ጉባኤ ላይ ሰብኮ ነበር። ይህን ለማረጋገጥ ከመጋቢዎቹ ማረጋገጫ ላገኝ ሞከርኩ። እነዚህ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ያሉአቸው ምዕመናን

ጥቂት ስለሆኑ እንዲህ ያለ ነገር ቢከሰት በመጋቢዎቹና በምዕመናኑ ቀርቶ እውጭ ባሉትም በብዙዎች ይታወቃል። ግን ከኤድስ እንደተፈወሱ ማረጋገጫ የሚያስጨብጡ በሽተኞች በሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት አልነበሩም። ለምሳሌ፥ ከሁለቱ የአንደኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንዲያ ያለ ሰው መኖሩን ስጠይቀው፥ 'አዎን' አለኝ። እርግጠኛ ፈውስም እንደሆነ ነገረኝ። ያ ሰው ስለ መፈወሱ በሐኪም የተረጋገጠ ወረቀት እንዳለው ጠየቅኩት። እንደሌለው ነገረኝ። ቀድሞ የኤድስ በሽተኛ ለመሆኑስ ማረጋገጫ እንዳለው ስጠይቅ አሁንም እንደሌለው ነገረኝ። እንግዲህ ይህ ሰው በኤድስ የተያዘም ሆነ የተፈወሰ ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም።

ይህንን ፈውስ ለማረጋገጥና እውነትነቱን ለማጣራት እንደምፈልግ ነግሬው ከሰውየው ጋር ለመገናኘት እንዲረዳኝ መጋቢውን ጠየቅኩት። ለዚህ ጥያቄ የሰጠኝ መልስ ጠንካራ፥ 'አይቻልም!' ነበረ። ለምን እንደማልችል የነገረኝም የይሉኝታ ችግር፥ የባሕላችን ምስጢር የመደበቅ ነገር፥ እንዲሁም ሰውየው በኤድስ መያዙን ሰዎች ካወቁበት ምን ይሉኛል ባይነቱ ነበር። 'የአገራችንን ባህል ታውቃለህ፤ ሰዎች እንደዚህ ያለ ነገር አይወድዱም። ደግሞም ይህ ሰውየው ያመነውንና የተቀበለውን ፈውሱን ማበላሸት ነው።' ነበር ያለኝ። መጋቢው ፈውሱን በደፈናው ያምናል። እንዴት እንዳመነ ስጠይቀው በሽተኛውን በግል ካጫወተው በመነሣት ሲመረመር የኤች አይ ቪ ካውንቱ ወይም በደም ሴሎች ውስጥ የሚቆጠረው የቫይረስ መጠን እንደቀነሰ በመናገሩ ነው። ይህ 'ካውንት' የሚባለው ደም ወስደው ሲመረምሩ በደም ውስጥ ያለው የቫይረሶቹ ቁጥር ሲጨምርና ሲቀንስ የሚሆነው ነገር ነው። ይህ ቁጥር አንዳንዴ ይጨምራል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ይቀንሳል። እንግዲህ ያ ሰው ተፈወሰ ከተባለ በኋላ በአንዱ ምርመራ ወቅት የቫይረሱ ካውንት ቀነሰ እንጂ እንዳልተፈወሰ ግልጽ ነው። ቀነሰ ማለት ቀነሰ ነው እንጂ ጠፋ አይደለም። ይህ ሰው ቀድሞም ኤድስ እንዳለበት ሳይታወቅ፥ ኋላም ተፈወሰ ተብሎ በጉባኤው ውስጥ ይገኛል።

እግዚአብሔር ፈዋሽ ነውና ቢፈውስ መደነቅ አለበት። የዚያኑ ያህል ደግሞ ያልተፈወሱትን እንደተፈወሱ የሚናገሩ ፈውሰኞች ስሕተታቸው ሊነገራቸው ይገባል። ችግሩ የፈውስ ስጦታ አለን ባዮቹ ብቻ አይደለም። ከበሽተኞችም ሳይፈወሱ የተፈወሱ

እየመሰላቸው የተሞኙ ጥቂት አይደሉም። አንዳንዶች በየዋኅነት ከኤድስ መፈወሳቸሁን ተቀበሉ ስለተባሉ ጉም እየዘገኑ ሳይመረመሩ የትዳር ጓደኛ ፈልገው እያገቡ ለሌላ ጠንቅ የሆኑ አሉ። አንዳንዶቹ ከልባቸው ያለመፈወሳቸውን እያወቁ ግን እንደተፈወሱ ሆነው ቀድሞ ያጡትን ተቀባይነት አግኝተው እየተደሰቱበት መጠቀሚያ ያደረጉትም አሉ። እንዲህ ያለ አንድ ደፋር ሰው አይቻለሁ። ደፋር ያልኩት በየዋኅነት ተፈውሻለሁ ብሎ የሚወዛወዝ ሳይሆን ሊያጭበረብርበት የሚሞክር መሆኑን በማረጋገጥም ነው።

የዚህ ሰው 'ፈውስ' ታሪክ እንዲህ ነው። በ1989 ዓመተ ምሕረት ታኅሣስ 13 ቀን በአዲስ አበባ ባለች አንዲት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን (ኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት) የአምልኮ ጊዜ አንድ ሰው ከኤድስ እንደተፈወሰ ለጉባኤው መሰከረ። ለፈውሱ የጸለየለት አገልጋይ (ወንጌላዊ ሞገስ መንግሥቱ) በዕለቱ ይሰብክ ነበርና ከስብከቱ ጊዜ ቀርሶ ለተፈወሰው ሰው በሰጠው ዕድል ነው ምስክርነቱ የተደመጠው። ሰውየው እንዴት በመሰለ አስደናቂ ሁኔታ ጌታ እንደፈወሰው መሰከረ። ጉባኤውም በተለመደው የተጋነነ ሆታና እልልታ ቤቱንም ዳሱንም ሞላው። በጊዜው በቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት ውስጥ እሠራ ነበርና የፈውሱን ዜና ሰማሁ። ይህንን የፈውስ ዜና ያካፈለን የክፍላችን ባልደረባና አንድ ቢሮ ውስጥ የምንሠራ የዚያችው የኅብረት አምባ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ወንድም ነው። ይህ ከሆነበት ቀጥሎ ባለው ሳምንት አጋማሽ ላይ ከሥራ ባልደረባዬ ከወንድዬ ዓሊ ጋር በመሆን በዚያችው በተፈወሰበት ቤተ ክርስቲያን ከዚሁ ከተፈወሰው ሰው ቀጠሮ ተይዞልን ቃለ መጠይቅ አደረግንለት። ከሕመሙ እንዲፈወስ የጸለየለትንም ሰው አነጋገርን። ሁለቱንም ያነጋገርነው እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ ነውና ይህ ነገር እውነት ከሆነ የእግዚአብሔር የፈውስ ሥራ አዋጅ ተብሎ ወንድዬ በሚያዘጋጃት በቃለ ሕይወት መጽሔት እንዲጻፍ፥ ካልሆነም፥ ውሸታም ፈውስ ነውና ከሐሰተኛ ፈውሰኞችና ተፈዋሾች ሰዎች እንዲጠነቀቁ ምዕመናንን ለማሳሰብ ነበር።

እንደ ተፈዋሹ ምስክርነት በጦር ሠራዊት ውስጥ በሰሜን ክፍለ ጦር ሲያገለግል ሳለ በበሽታው እንደተለከፈና በተጨማሪም የሳንባ በሽተኛ መሆኑንም ነገረን። የሳንባ

በሽተኛ ለመሆኑ ከሳንባ ነቀርሳ ክሊኒክ የተሰጠውን መታወቂያ ለማረጋገጫ አሳይቶናል። ከዚህኛው ሕመም መፈወሱን ግን አልተናገረም ወይም ማረጋገጫ አላሳየንም። በዚያው የሳንባ ሕመምተኛ መሆኑን የሚያሳየው መታወቂያ ላይ የተጻፈው በሐኪም እንደሆነ የነገረን የኤድስ በሽተኛ መሆኑን የሚመሰክር የእጅ ጽሑፍም አለበት። ሰውየው ስለ ሕመሙ በሰፊው መሰከረልን። ከሦስት ሳምንታት በፊት በቤተ ክርስቲያኒቱ በሚደረገው መደበኛ የዐርብ የጸሎት ጊዜ ተገኝቶ ሳለ አገልጋዩ እጁን ጭኖ ሲጸልይለት ኃይለኛ እንደ ኮረንቲ ያለ ንዝረት እንደተሰማውና በሰውነቱ ላይ የነበረው ቁስል በማግስቱ እንደደረቀ ነገረን። ወደ ሐኪሞቹም ዘንድ ሄዶ መፈወሱን እንደነገራቸውና እነርሱም እንደገና መርምረው ነጻ መሆኑን እየተገረሙ እንደነገሩት አወጋን። አስፈላጊ ማስታወሻዎችንና ምስሎችን ከወሰድን በኋላ ለሚቀጥለው ቃለ መጠይቅ ከሐኪሞቹ የተሰጠውን ከኤድስ ነጻ የመሆኑን ማረጋገጫ ወረቀት እንዲመጣና እንዲያሳየን፥ የሐኪሞቹንም ስምና አድራሻ እንዲሰጠን ተስማምተን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

በቀጣዩ ቀጠሮ በተባለው ሰዓት ቃለ መጠይቁን ያደረግነው ሁለታችን (እኔና ወንድዬ ዓሊ) እንዲሁም የክፍላችን አለቃ (ጌታቸው በለጠ) እና በመጀመሪያ ታሪኩን ያካፈለን የመሥሪያ ቤታችን የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ሠራተኛ (ሰሎሞን ደጀኔ) ተያይዘን ሄድን። በመጀመሪያው ቃለ መጠይቅ ወቅት የያዝናቸው ውሸት እንደሆኑ የተረዳናቸው ነጥቦች ነበሩ። እነዚያንም ማረጋገጥ ይኖርብን ነበር። በቀጠሮ ጊዜና በቦታው (በኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን) ተገኝተን ሁለት ሰዓት ያህል ከጠበቅነው በኋላ ስላልመጣ ትተን ወደ ቢሮችን ተመለስን። ከተመለስን በኋላ በዚያው ቀን ስለ እርሱ ሌላ አስደንጋጭ ነገር ሰማንና ያንንም ለማስረገጥ በሳምንቱ ውስጥ አስፈልገን ልናገኘው ሞከርን፤ አልተሳካልንም።

የዚህኛውን የአዲሱን አስደንጋጭ ነገር እውነትነት ለማረጋገጥ ግን ከሚያውቁት ሦስት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ጋር ባደረግነው ቃለ መጠይቅ ይህ ሰው ከዚያ ጊዜ ሁለት ዓመታት በፊት በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ከኤድስ ተፈወሰ የተባለለትና እርሱም ተፈወስኩ ብሎ ሰፊ አድናቆን ያተረፈ፥ በአንድ ክርስቲያናዊ

ጋዜጣም ታሪኩ የተጻፈለትና ብዙ የዋህ ክርስቲያኖችም በተለያዩ መንገዶች የገንዘብና ሌሎችም እርዳታ ሲያደርጉለት የቆየ ሰው መሆኑን፥ አሁን ያ እርዳታ ከወዲያ በኩል ሲመነምን ወደዚህችኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ተመሳሳይ ድራማ ሊሠራ እየሞከረ መሆኑን ነገሩን። ደፋሩ ሰው ከዚያ በኋላ የውኃ ሽታ ሆነ፤ ልናገኘው አልቻልንም። እንደፈወሰው ለመሰለው አገልጋይ ሰው፥ ወንጌላዊ ሞገስ፥ ግን ጉዳዩን ስንገልጥለትና ሰውየው አጭበርባሪ እንደሆነና አሁንም እንዳልተፈወሰ ስንነግረው የእርሱን ጸጋ እንዳጣጣልንበት ብቻ ነበር ጉዳዩን የወሰደው እንጂ የአደጋው ግዝፈት አልታየውም።

የውሸት ፈውሶችን ያለ ፈቃድ እያባዙ የሚሸጡ ፈውሰኞች ዝም መባል ያለባቸው እስከ መቼ ነው? ፈውሰኞችስ በማይረጋገጡ በሽታዎች ብቻ ላይ ተጣብቀው የሚቀሩት እስከ መቼ ይሆን? የውሸት ፈውሶች በፈዋሾችም ይደረጉ ወይም በተፈዋሾች፥ ችግራቸው ቶሎ የሚቀረፍ አይደለም። ከፈውሱ ያለመኖር አካላዊ ጉስቁልና ባሻገር ስሜታዊና መንፈሳዊ ኪሳራ አለበት፤ በማያምኑትም ዘንድ ሳይቀር የሚፈጠር የስም መጉደፍና ሞራላዊ ዝቅታ ይከተላል። ይህ ደግሞ በተራው የወንጌል ሩጫን የሚያስዘግምና ምስክርነትን የሚያጎድፍ ነው።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኬንያ ውስጥ እንዲህ ያሉ የውሸት ፈውሶች እጅግ እየበዙ ውሸትነታቸው በአማኞችም በዓለማውያንም ዘንድ በግልጽ እየታየ መጥቶ የቤተ ክርስቲያን መነወሪያና የእግዚአብሔር ስም መሰደቢያ ሆኖ ነበር። The Nation የተባለ የአገሪቱ ጋዜጣ ስለነዚህ የተአምር ፈውሰኞች እነዚህን የተአምር ነጋዴዎች አስወግዱልን በሚል ርእስ አንድ መጣጥፍ ጽፎ ነበር። በውስጡ ከተጻፈው መሐል፥

> እነዚህ ዳንን የሚሉ ሰዎች እነማን ናቸው? ከየት ነው የመጡት? ለምንድነው ሁሌ እንግዳና የማይታወቁ የሚሆኑትና ከዚያ በፊት ያልታወቁ ከዚያም በኋላ የማይገኙ የሚሆኑት? እንደሚታወቀው እያንዳንዲቱ የኬንያ ከተማ የሚታወቁ ዐይነ ስውር ለማኞችና አካለ ስንኩላን አሉአት። ከእነዚህ አንዳቸው ተፈውሰው ቢሆን የከተማዋ ነዋሪዎች ሁሉ ተአምር መፈጸሙን ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህ ታላላቅ ወንጌላውያን መጥተው ሲሄዱ ዕውርና አንካሳ ለማኞቻችንን እዚያው የነበሩበት ነው የምናገኛቸው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ተአምራዊ ፈውስ ልማድ ከቶም አይደለም። እነዚህ ወንጌላውያን በስሙ የሚነግዱበት

ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራቱን ይፈጽም የነበረው በስውር አልነበረም፤ ደግሞም ሰዎች እውነትነቱን እንዲያረጋግጡት አይከለክልም ነበር። በሉቃ. 5፥12 ኢየሱስ ለምጻሙን ከፈወሰ በኋላ ሰውየው ወዲያው ሄዶ ራሱን ለካህናት እንዲያሳይና መፈወሱ እንዲረጋገጥ ነበር የላከው።[1]

ይህ ከአማኙም ከአላማኒውም ሰፊ ተነባቢ ያለው ብሔራዊ ጋዜጣ ነው። ፈውሶቹ ሐሰተኞች ከሆኑ የሚያስተጋባው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።

ወደ ኤድስ ስንመለስ ደግሞ ቀሳፊነቱና ተዛማችነቱ የፈውሱን እርግጠኛነት የሚያስጠይቅ ቢሆን ይህን ማረጋገጫ መጠየቅ የሌሎችን እምነትና ፈውስ እንደ ማፍረስ፥ እንዲሁም እንደ ነውር መቆጠር የለበትም። ኤድስን ሰውም ይሥራው፥ የሰማይ ቁጣም ይሁን ከዘመናችን ክፉ መቅሰፍቶች አንዱ መሆኑ እሙን ነው። እግዚአብሔር ፈዋሽ አምላክ መሆኑን ሳንዘነጋ ኤድስን እንደ ሕመም ወይም እንደ ደዌ ካየነውና ፈውስ ተደረገ ከተባልን እነዚያ ተፈወሱ የተባሉ ሰዎች እንደዋዛ ከመደባለቃቸው በፊት ማረጋገጥና ማረጋገጫ መጠየቅ እንደ ከሃዲነት ወይም እንደ እምነት አፍራሽነት መታየቱ አግባብ አይደለም። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ከላይ በኬንያው ጋዜጣም እንደ ምሳሌ የተጠቀሰው በሉቃ. 5፥12-14 ያለው የጌታ የፈውስ አገልግሎት ክፍል ነው። ይህን ክፍል ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር እንመልከተው።

12፥ ከከተማዎችም በአንዲቱ ሳለ፥ እነሆ፥ ለምጽ የሞላበት ሰው ነበረ፤ ኢየሱስንም አይቶ በፊቱ ወደቀና፥ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ፥ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው። 13፥ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው። 14፥ እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን፥ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መሥዋዕት አቅርብ አለው።

ጌታ በገሊላ አካባቢ ካሉት ከተሞች በአንዲቱ ሳለ አንድ ለምጻም መጣ። እንደዛሬው ሁሉ በዚያን ዘመን እስራኤልም ሁለት ዓይነት ለምጽ ነበር። አንደኛው የቆዳ ለምጽ ነው። የላይኛውን የቆዳ ቀለም እየበላ የሚሰፋ፥ ጥቁርና ጠይሞችን ቀይ፥ ቀዮችን ደግሞ ነጭ የሚያደርግ የቆዳ በሽታ ነው።

[1] *Outlaw these Miracle Merchants:* The Nation (Kenya), Sep, 29, 2001.

ሁለተኛው ግን ከቆዳ አልፎ ወደ ሥጋ ውስጥ የሚገባ ከሰውነት ጫፎች በአንዱ ወይም በጥቂቱ፥ በእጅ ወይም በእግር ጣት፥ በአፍንጫ፥ በጆሮ ጫፎች ይጀምርና ወደ መሐል እየሰረሰረ የሚሄድ፥ ሥጋን ሁሉ እየበላ የሚዛመት የነርቭ በሽታ ነው። ጣቶች አልቀው የእጅ ወይም የእግር ጉቶ ብቻ እስኪቀር ድረስ የሚጎምድ፥ የሚቆምጥ በሽታ ነው። የዚህ በሽታ ዋና ክፋት ነርቮችን ስለሚገድል በሽተኛው ሕመሙ አይሰማውም። እየቆሰለ፥ እየተቆረጠ፥ እየተወጋ ምንም አይሰማውም። በሕይወት እያሉ አካል ማለቅ፥ መሞት ይጀምራል። ቁምጥና ወይም የሥጋ ደዌ የሚባለው ይህ በሽታ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ሁለቱም ለምጽ ተብለው ነው የተጠሩት።

ለምጽን ወይም ቁምጥናን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የተሰጠ ሰፊ ሕግ ይገኛል። ከድንጋጌዎቹ መካከል አንዱ ከማኅበረሰቡ እንዲለይ የሚያዝዘው ነው። በተለይ ዘሌ. 13፥45-46 ይህ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀደደ፥ ራሱ የተገለጠ፥ ከንፈሩ የተሸፈነ እንዲሆን፥ ሰው እንዳይቀርበውና እንዳይነካው ለማስጠንቀቅ፥ ‘ርኩስ ርኩስ ነኝ!’ እያለ እንዲናገር፥ መኖሪያው ከሰፈር ውጭ ሆኖ ብቻውን (ወይም ከብጤዎቹ ጋር) እንዲኖር ያስጠነቅቃል። ከኅብረተ ሰቡ ወጥቶ፥ ከቤተ ሰብ ተለይቶ፥ ተሰድዶ ለብቻው ይኖራል። የማንም ትከሻ አይገፋውም፤ የማንም እጅ አይዳስሰውም፤ ማንም ለሰላምታ አያቅፈውም። ተጋፍቶ መኖር ትልቅ በረከት መሆኑን የሚያውቅ ሰው ነው። ይህ ለምጽ ወይም ቁምጥና ኃፍረት፥ ፍርሃትና ድንጋጤ የሞላበት በሽታ ነው። ጥንትም ዛሬም እንደሚነገረው እነዚህን በሽተኞች የሚጎዳቸው ከአካላዊው ጉዳት ይልቅ ሕሊናዊውና ስነ ልቡናዊው ስቃይ ነው። ሰው ሁሉ ሲያያቸው የሚዘገንነው፥ የማይቀርባቸው፥ የማይነካቸው፥ ከሩቅ የሚሸሻቸው ናቸው። ለእንደነዚህ ያሉ ሰዎች ሰዎችን ከመንካትና በሰዎች ከመነካት የበለጠ ምንም የሚያስደስታቸው ነገር የለም።

እንዲህ ያለው ለምጻም ሰው ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው። ይህ ሰው በቆዳው ለምጽ ሳይሆን በቁምጥናው ለምጽ የተያዘ ነው። ለምጻም ሳይሆን ለምጽ የሞላበት ነው የተባለው። ይህ ለምጻም ሰው ሊነካው ቀርቶ ማንም የማይቀርበው ዓይነቱ ለምጻም ነው። ስለ ኢየሱስ የነበረው እውቀት ግን በቂ ነበር። ‘መምህር ሆይ’ ሳይሆን፥ ‘ጌታ ሆይ’ ነበር ያለው፤ የጌታን ጌትነት ያወቀ፥ ያመነና የተቀበለ ይመስላል። ኢየሱስ

ሊያነጻው እንደሚችል ወይም ችሎታ እንዳለው አውቆአል፤ ግን ሊያነጻው እንደሚወድ እርግጠኛ አይመስልም። በእግዚአብሔር ዘንድ መቻልና መውደድ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እርሱ ሁሉን ቻይ ነውና ሁሉን ማድረግ ይችላል። የሚችለውን ሁሉ ግን ያደርጋል ወይም ሊያደርግ ይወድዳል ማለት አይደለም። ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር መፈወስ ይችላል፤ ነገር ግን መፈወስ ይችላል ማለት ፈቃዱ ሁሌ ፈውስ ነው ማለት አይደለም። የፈቃዱን እውቀት የማወቅ አስፈላጊነት እዚህ ላይ ነው። ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወድቆ ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ አለው። ጥያቄ አይደለም። ብትወድ፥ ብትፈልግ ትችላለህ ማለቱ ነው። ይህ ሰው የማይቀርበውና ወደ ሰው መቅረብ የሌለበት ሰው ነው። ሁሉ የሚጸየፉት፥ ወደ ሰዎች መካከል እንዳይቀርብ ሕጉም የሚያግደው ይህ ሰው ሰውን ሁሉ አልፎ ወደ ኢየሱስ መጣና በፊቱ ወደቀ።

እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ እወዳለሁ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው። በብሉይ ሕግ ለምጻምን መንካት ርኩስን መንካት ነው። ርኩስን መንካት መርከስ ነው። አይሁድ ላለመርከስ በጣም ይጠነቀቃሉ። ጌታ ግን ነካው። ዳሰሰው። የማይነካውን ነካ! መንካት ብቻ አይደለም፤ ሰዎች ሁሉ እጃቸውን ወደሚሰበስቡበት ሰው እጁን ዘረጋና ዳሰሰው። እወዳለሁ ንጻ ብሎ ቃልን ተናገረ። ሳይነካው ቃልን ብቻ መናገሩ ሊፈውሰው ይችል ነበር። እርሱ ግን ከዚያም ያለፈ አደረገ። በጌታ ዘንድ ፍቅር ከሕግ በላይ ነው። የዳሰሰው ሕጉን ለመሻር ሳይሆን ፍቅርን ለመግለጥ ነው። ለፈውሱ ቃልን መናገሩ በቂ ቢሆንም የሰውየውን ጥልቅ የፍቅር ናፍቆት፥ የመድዳሰስ ፍላጎት ግን ቃልን በመናገሩ አይደርስም። ስለዚህ ይህንን ለመድረስ ዳሰሰው። ይህ ከቆዳውና ከሥጋው ያለፈ የልብ ቁስል ፈውስ ነው። እሱና ጌታ የሚያውቁት የውስጥ ፈውስ ነው። ኋላ ሄዶ ራሱን ለካህን ቢያሳይም ካህኑ የተፈወሰ ሥጋውን እንጂ የተጠገነ ልቡንና ሙሉ የሆነ እሱነቱን አያይም። ይህ ድንቅ ጌታ ነው። ይህ ድንቅ እውነት ነው። ዛሬም ያልተለወጠ ባሕርዩ ነው።

*እርሱ ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን፥ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለመንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መሥዋዕት አቅርብ አለው።*

በመጀመሪያ ለማንም እንዳይናገር አዘዘው። ይህን ያለው ምናልባት ወሬው ያለልክ ተዛምቶ የወሬና ተአምር የማየት ናፍቆት ያላቸው ሰዎችን ስብሰባ ለማስቀረት ይሆን? ቀጥሎም ራሱን ለካህን እንዲያሳይና መሥዋዕት እንዲቀርብ አለው። ይህ መሥዋዕት በዘሌ. 14 የተጠቀሰው ነው።

ራሱን ለካህን ማሳየቱ አስፈላጊ ነበር። ካህን በብሉይ ኪዳን የፈውስ አስረጋጭ፥ ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ፥ መፈወሱን የሚያረጋግጥ፥ ወይም በዘመናዊ ቋንቋ ነጻ ነው የሚል የምስክር ወረቀት እንደሚሰጥ ሐኪም ነው። ለምጹ መጥፋቱ በሰውነቱ ይታያል። ግልጽ ነው። ማኅበረ ሰቡ ግን ሊቀበለው ይከብደዋል። አሁንም ለምጻም ይመስለዋል። ኢየሱስ በሽታውን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ግንኙነቱንም ሊፈውስ ወደ ካህን ላከው።

አንዳንድ ሰዎች ከተፈወሱ በኋላ ሄደው ለሐኪም እንዲታዩ ሲነገራቸው አገር ጥለው መጥፋት ያሰኛቸዋል። ለምን ሲባሉ እምነት ማጣት ይመስላቸዋል። ከላይ የተጠቀሰው ከኤድስ ተፈወሰ የተባለው ሰው መጋቢ ያ ሰው መፍፈወሱን መጠየቁ እምነቱን መናድ እንደመሰለው ማለት ነው። መጠየቅና ማረጋገጥ የነበረበት ካህን እርሱ ራሱ ነበር፤ ግን እርሱ ራሱ እንዳይፈተሽ ተከላካይ ሆነ። የፈወሱአቸው ሰዎች ወይም፥ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ የሚባለው ነገር ራሱ፥ ስለ እምነት ረቂቅና የማይጨበጥ ትምህርት ሰጥተዋቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም እንዲህ ያለ ነገር ባናገኝም ፈውሰኞች ተፈዋሾቹን፥ ለመፈወስ እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን፥ ቢፈወሱም እንኳ ከተጠራጠሩ በሽታው እንደሚመለስባቸው በመናገር ያስፈራራሉ። ስለዚህ ወደ ሐኪም ሄዶ መፈወስን ማረጋገጥ በደል መስሎአቸው፥ ‘ተፈውሰሃል’ ተብለው፥ ‘ተፈውሻለሁ’ ብለው ይኖራሉ። በድንገትና በፍጥነትም ይሰናበታሉ። ‘ምን ሆነ?’ ሲባል፥ ‘ወደ አምላኩ ተሰበሰበ።’ ይባላል። እርግጥ በክርስቶስ ካመነ ወደ አምላኩ ተሰብስቦአል። ግን ምን ሆኖ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ አይሰጥጥም። ጥያቄው እንዲነሣም አይፈለግም። ስለዚህ ያልተፈወሱ ሰዎች፥ ‘ተፈወሱ’ ሲባል ጠንቃቃ እንሁን። ይህ አሳብ በመንፈስ ቅዱስ እና ካሪዝማዊ ቀውሶች መጽሐፍ ውስጥ ‘የፈውስ ቀውስ’ በተባለው ንዑስ ርእስ ስር በስፋት ተጽፎበታል።

በጌታ የተፈጸመው ተአምር ምንም ያልጎደለው ተአምር ነው። አድራጊው ደግሞ ራሱ ጌታ ነው። ያ ለምጻም ከተፈወሰ፥ 'ተፈውሰሃል' ብቻ ብሎ ለምን አልተወም? ለምን ሄዶ ራሱን ለካህን እንዲያሳይ አለው? ምክንያት ነበረው። ድውዩ ለራሱ ተፈውሶአል፤ ለሌላውም ፈውሱን ማረጋገጥ አለበት። ፈውስ የሆነላቸው ሰዎችም በሰውነታቸው አውቀውታል። አንዳንዱ ፈውስ ግን ዝም ብሎ ከመደባለቅ በፊት ሌላ ማረጋገጫ ይፈልጋል። ያለ ጥርጥር የኤድስ ፈውስ ከነዚህ ማረጋገጫ ፈላጊ ፈውሶች አንዱ ነው። ያለዚያ የኤድስ ፈውስ ሳይሆን የኤድስ ቀውስ ነው።